.164

# የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ

ስለ ራሳቸው ደኅንነት የሚሰማቸው ሰዎች
ከፍተኛ ምርት ያስገኛሉ ።

በኬኔት ብላንቻርድ ፒ. ኤች. ዲ.
እና
በስፔንሰር ጆንሰን ኤም. ዲ.



ትርጉም
ታዴ ሊበን

# የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ


በኬንት ብላንቻርድ ፒ. ኤች. ዲ.

እና

በስፔንሰር ጆንሰን ኤም. ዲ.



Are Gifts More Precious Than Jewels.
ያበረከተው / Donated By


ትርጉም ታዲ ሊበን


ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፹፪

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ) Tel. ) 11 27 19
ፖ. ሣ. ቁ.) P. O. Box ) 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል—ሉቃስ አማረ

# ማውጫ

ተራ ቁ. — ገጽ


1. መግቢያ ከደራሲዎቹ 5
2. ፍ ለ ጋ - - - - - - - - - - - 7
3. የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ - - - 12
4. የመጀመሪያው ምሥጢር የአንድ ደቂቃ ግቦች - - - - - - - - - - - 21
5. የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ሲጠቃለል - - 30
6. ሁለተኛው ምሥጢር የአንድ ደቂቃ ሙገሳ - - - - - - - - - - - 32
7. የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ሲጠቃለል - - 40
8. ግ ም ገ ማ - - - - - - - - 43
9. ሦስተኛው ምሥጢር ፥ የአንድ ደቂቃ ግሣፄ - - - - - - - - - - - 46
10. ያንድ ደቂቃ ግሣፄ ማጠቃለያ - - - 56
11. የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ያስረዳል - 58
12. የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ለምን ስኬታማ እንደሚሆን - - - - - - - - 62
13. የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ለምን ውጤት እን ሚያስገኝ - - - - - - - - - 72
14. የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ - - - - - - - - - 84
15. ወጣቱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ሆነ 97
16. የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ማስታወሻ አጭር ማጠቃለያ - - - - - - 98
17. ለራስህ የሚቀርብ ስጦታ - - - - 100
18. ለሌሎች የሚሰጥ ስጦታ - - - - - 103

# መ ግ ቢ ያ

በዚህች አጭር የፈጠራ ሥራ ያቀረብንላችሁ ሰዎች እንዴት በሠመረ መንገድ አብረው መሥራት እንደሚችሉ ከሕክምና ሙያና ከሥነ—ባሕሪያት ምርምር ያካበትነውን ሰፊ ዕውቀት ነው ።

«በሠመረ» መንገድ ስንል ፡ ሰዎች ለራሳቸው ፡ ለድርጅታቸውና አብረዋቸው ለሚሠሩት ለሌሎች ሰዎች ደኅንነት እያሰቡ ፡ እንዴት አመርቂ ውጤት ማስገኘት እንደሚችሉ ማለታችን ነው ።

ይህች በተረት መልክ የቀረበችና የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ የተሰኘች መጽሐፍ ይዘት ባለሞያ ዎች ያስተላለፉልንና እኛም በየበኩላችን የቀሰም ናቸውን ትምህርቶች አንባቢ መረዳት በሚችልበት በቀላል ዘዴ ያከተተች ናት ። ለነዚህ የዕውቀት ምን ጮች ከፍተኛ ግምት እንሰጣለን ። አብረውን የሚ ሠሩ ሰዎች እኛኑ የጥበብ ምንጫቸው አድርገው እንደሚመለከቱ እንገነዘባለን ።

ስለዚህ ፡ ሥራ አስኪያጆች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸውን ተግባራዊ ዕውቀት በየዕለቱ ሥራ አመራር ክንዋኔያቸው እንደሚጠቀሙበት

ሙሉ እምነት አለን ። ታላቋ የጥንታዊቷ ቻይና ጠቢብ ፤ ኮንፊውሽስ ፤ እንደሚመክረን «የዕውቀት ሁሉ መሠረት ፤ በመጀመሪያ ዕውቀቱን ማግኘት ፤ ከዚያም በተግባር ማዋል ነው ።»

ማንም ሥራ አስኪያጅ ፤ ከየአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር የሚማረውን ተግባራዊ እንደሚያደርግና በውጤቱም እርሱና አብረውት የሚሠሩት ሰዎች የአእምሮና የአካል ጤንነትን ፤ ተደሳችነትንና ውጤታማ ሕይወትን እንደሚጐናጸፉ ተስፋ እናደርጋለን ።

ኬኒት ብላንቻርድ ፒ.ኤች ዲ
ስፔንሰር ጆንሰን ኤም.ዲ



# ፍ ለ ጋ

በአንድ ወቅት ባለሟል ሥራ አስኪያጅ ለማግኘት ታጥቆ የተነሣ አንድ ብልህ ወጣት ነበር ።

ለእንዲያ ያለው ሥራ አስኪያጅ ተቀጥሮ ለመሥራት ይመኛል ። እርሱ ራሱ ጐበዝ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ያልማል ።

የዚህን ዐይነት ሥራ አስኪያጅ ለማግኘት ለበርካታ ዓመታት ዓለምን ከዳር እስከ ዳር ዞረ ።

አነስተኛ ከተሞችንና የኃያላን መንግሥታት መዲናዎችን ጐበኘ ።

በየተዘዋወረባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ሥራ አስኪያጆችን ፤ አስተዳዳሪዎችንና ወታደራዊ መኰንኖችን ፤ የሕንፃ ተቆጣጣሪዎችንና የኮርፖሬሽን መሪዎችን ፤ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮችንና የማምረቻ ኃላፊዎችን ፤ የሱቅና የመጋዘን ፤ የባንኮችና የሆቴሎች ፤ የምግብ ቤት ኃላፊዎችን ፤ ወንዶችንና ሴቶችን ፤ ወጣቱንና አዛውንቱን ለማነጋገር ዕድል አገኘ ።

በጐበኘቱ ወቅት የተለያዩ ሀይነት ቢሮዎችን ፤ ትንንሽና ትልልቅ ፤ በዘመናዊ ዕቃ የተሞሉና

እና የመሰሉ ፡ መስኮቶች ያሏቸውና የሌላቸውን ሁሉ አየ ።

ሰዎች ሰዎችን እንዴት እንደሚመሩ ሰፊ ግንዛቤ ማግኘት ጀመረ ።

ይሁን እንጂ ፡ በተመለከታቸው ነገሮች ሁሉ አይረካም ነበር ። ሠራተኞቻቸው የቆረቆዙ ፡ ድርጅቶቻቸው የከበሩ የሚመስሉ ብዙ 'ጠንካራ' ሥራ አስኪያጆች አጋጥመውታል ።

እነዚህን ሥራ አስኪያጆች አንዳንድ የቅርብ ረዳቶቻቸው ጥሩ የሥራ መሪዎች ናቸው ብለው ይገምቷቸዋል ። ነገር ግን የብዙዎች የበታች ሠራተኞቻቸው ሐሳብ ደግሞ የተለየ ነበር ።

ይህ ወጣት ፡ እነዚህን 'ጠንካራ' ናቸው የሚባሉትን መሪዎች በየቢሮዎቻቸው ውስጥ ባነጋገራቸው ቁጥር ፡ «ለመሆኑ ምን ዐይነት የሥራ መሪ ነኝ ብለው ራስዎን ይገምታሉ?» የሚል ጥያቄ ያቀርብላቸው ነበር ።

መልሶቻቸው እምብዛም ልዩነት አልነበራቸውም ። «እኔ ቆራጭ ፈላጭ ሥራ አስኪያጅ ነኝ ፤ ሁኔታዎች በቁጥጥሬ ሥር ናቸው» የሚል ምላሽ ነበር የሚያገኘው ። «የማልበገር » ፡ «ሐቀኛ» «ትርፍ ላይ የማተኩር ነኝ» በማለት ራሳቸውን የሚያሞካሹ ነበሩ ።

ጉራቸውንና ለውጤት መስገብገባቸውን አዳመጠ ።



ይህ ወጣት 'ጥሩ ሥራ አስኪያጆች ናቸው ከሚባሉ ግን ፤ ሠራተኞቻቸውን እየካቡ ድርጅቶቻቸውን ያቆረቆዙ ከሚመስሉ መሪዎችም ጋር ተገናኝቷል ።

አንዳንድ የበታች ሠራተኞቻቸው ጥሩ ሥራ አስኪያጆች ናቸው ይላሉ ። የበላዮቻቸው ግን የራሳቸው ጥርጣሬ አላቸው ።

እነዚህ 'ጥሩ' ሥራ አስኪያጆች የሚባሉት ሰዎች ወጣቱ ለሚያቀርብላቸው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ «እኔ ዲሞክራቲክ ነኝ» «ተሳታፊ» ፡ «ደጋፊ» «ትሁት» ፡ «ርኅሩኅ» በማለት ስለ ራሳቸው ይናገራሉ ።

ጉራቸውንና ለሰው ያላቸውን ተቆርቋሪነት አዳመጠ ። ግን ግራ ተጋባ ።

ከሥራ አስኪያጆች አብዛኞቹ ወይ በውጤት ላይ የሚያተኩሩ ወይ ደግሞ ስለሰዎች የሚያስቡ መስለው ታዩት ።

በሥራ ውጤት ላይ የሚያተኩሩት ሥራ መሪዎች ብዙውን ጊዜ «ቆራጭ ፈላጭ» የሚባል ሥያሜ ሲሰጣቸው ፡ የሰዎችን ምቾት የሚያስቀድሙት ደግሞ «ዲሞክራቲክ» ተባሉ ።

ወጣቱ «ቆራጭ ፈላጭ» እና «ዲሞክራቲክ» ስለተባሉት ሥራ አስኪያጆች አሰላሰለ ። ውጤታማነታቸው ከፊል ብቻ መሆኑን አስተዋለ ። 'እንደ

ግማሽ ሥራ አስኪያጆች የሚቆጠሩ ናቸው’ አለ
በልቡ ።

ደክሞና ተስፋ ቆርጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።
ፍለጋውን ቀደም ብሎ ባቋረጠ — ግን እንዲ
ገፋበት ያበረታታው አንድ ነገር ነበር ። ይኸውም
ምን እንደሚፈልግ በትክክል ማወቁ ነው ።

«ውጤታማ ሥራ አስኪያጆች ራሳቸውንና አብ
ረዋቸው የሚሠሩትን ሠራተኞች ሚዛናዊ በሆነ ዘዴ
በመምራታቸው ድርጅቶቻቸውም ሆኑ ሠራተኞቻ
ቸው ተጠቃሚዎች ይሆናሉ» የሚል ሐሳብ ነበረው ።

ወጣቱ እንዲህ የመሰለ ሥራ አስኪያጅ ለማግ
ኘት በየቦታው ተንከራተተ ። ነገር ግን ያጋጠሙት
በጣም ጥቂቶች ሆኑበት ። እነዚህም ቢሆኑ ምሥ
ጢራቸውን ሊያካፍሉት አልፈቀዱም ። አንድን
ሰው ውጤታማ ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን የሚያ
በቃውን ምሥጢር ምናልባት ጨርሶ ሊደርስበት
የማይችል መስሎ ታየው ።

እንዳጋጣሚ ካለበት ከተማ አጠገብ ስለሚገኙ
አንድ አስደናቂ ሥራ አስኪያጅ ግሩም ግሩም ታሪ
ኮች ሲነገር መስማት ቻለ ። ሰዎች ተቀጥረው ሊሠሩ
ላቸው መፈለጋቸውንና ባኅብረትም ከፍተኛ ምርት
የማግኘታቸው ዜና ከጆሮው ደረሰ ። የሚባልላቸው
ሁሉ እርግጥ መሆኑን ወጣቱ ለማወቅ ጓጓ ። እርግጥ
ከሆነም እኚህ ሥራ አስኪያጅ ምስጢራቸውን ሊያ
ካፍሉኝ ፈቃደኛ ይሆኑ ይሆን የሚል ጥርጣሬ አደ
ረበት ።



በአድናቆት ተውጦ ቀጠሮ ለመቀበል ለሥራ
አስኪያጁ ጸሐፊ ስልክ አደረገ ። ጸሐፊዋም ወዲያው
ከሥራ አስኪያጁ ጋር አገናኘችው ።
እኚህን ልዩ የሆኑ ሥራ አስኪያጅ መቼ
ማነጋገር እንደሚችል ቀጥሮ ፣ ሥራ አስኪያጁም
ከረቡዕ ጥዋት በስተቀር በዚህ ሳምንት በማንኛውም
ጊዜ ላነጋግርህ እችላለሁ ። የሚመችህን ጊዜ ምረጥ»
አሉት ። ወጣቱን ሣቅ አፈነው ፤ ምክንያቱም የእኚህ
አስደናቂ ሥራ አስኪያጅ አባባል እንግዳ ሆነበት ።
ምን ዐይነት ሥራ አስኪያጅ ነው ይህን ያህል የተ
ትረፈረፈ ጊዜ የሚኖረው? ወጣቱ ግርም ብሎታል ።
በአንድ ዕለትም ሊያነጋግራቸው ሔደ ።

## የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ

ወጣቱ ከቢሮው ሲደርስ ሥራ አስኪያጁ ቆመው በመስኮት ወደ ውጭ ሲመለከቱ አገኛቸው ። የመሳል ድምፅ ሲያሰማ ሥራ አስኪያጁ ዞር ብለው ፈገግታ አሳዩት ። ወጣቱን እንዲቀመጥ ጋበዙት ፡ «ምን ልርዳህ?» የሚል ጥያቄም አቀረቡለት ።

ወጣቱም ፡ «ሠራተኞችዎን እንዴት እንደሚመሩ ጥቂት ጥያቄዎች እንዳቀርብ ቢፈቅዱልኝ?» አላቸው ።

ሥራ አስኪያጁም በሙሉ ፈቃደኝነት «አዝን በዋ!» ሲሉ መለሱለት ።

«እሽ ፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከሠራተኞችዎ ጋር አዘውትረው ስብሰባዎችን ያካሒዳሉ?»

«አዎን ፥ በሚገባ እንጂ! በሳምንት አንድ ጊዜ ረቡዕ ከ3.00 እስከ 5.00 ሰዓት ስብሰባ እጠራለሁ ። ቀጠሮ ስትጠይቀኝ ረቡዕ ጥዋት አይመቸኝም ያልኩህም በዚህ ምክንያት ነው ።»

«በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ምንድን ነው የምታከናውኑት?» በማለት ወጣቱ ጥያቄውን ቀጠለ ።



«ሠራተኞቹ ባለፈው ሳምንት ያከናወኑትን ፡ ያጋጠማቸውን ችግሮችና ወደፊትም ማከናወን የሚገባቸውን ሥራዎች ሲገመግሙና ሲተነትኑ አዳምጣለሁ ። ከዚያ በኋላ ለሚቀጥለው ሳምንት የምንመራበትን ዕቅድና የክንውን ስልት በጋራ እናዘጋጃለን ።»

«በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ የሚተላለፉትን ውሳኔዎች እርስዎና ሠራተኞችዎ ተግባራዊ ለማድረግ ትገደዳላችሁ?»

«እንዴታ! እንገደዳለን» ሲሉ አጠንክረው መለሱለት ሥራ አስኪያጁ ። «ግዴታ ከሌለብንማ ስብሰባ መጥራቱ ምን ፋይዳ አለው?»

«እንዲያ ከሆን ተሳታፊ ሥራ አስኪያጅ መባልዎ ነው ፡ አይደል?» በማለት ጠየቀ ወጣቱ ።

«እንዲያውም ፡ ሠራተኞቹ ውሳኔ ሲያስተላልፉ ጣልቃ መግባቱን አላምንበትም» አሉት ሥራ አስኪያጁ ።

«ታዲያ መሰብሰባችሁ ለምኑ ነው?»

«ቀደም ብዬ ገልጬልሃለሁ ። የተናገርኩትን እንድደጋግም አታድርገኝ ። የእኔንም የአንተንም ጊዜ ማባከን ይሆናል ። እዚህ ያለነው ውጤት ለማግኘት ነው» በማለት ሥራ አስኪያጁ ንግግራቸውን ቀጠሉለት ። «የዚህ ድርጅት ዓላማ ቅልጥፍናን ማሳደግ ነው ። በመደራጀታችንም ይበልጥ አምራቾች ሆነናል ።»

«አሃ! ለምርታማነት ቅድሚያ ይሰጣሉ ማለት ነው ። ስለዚህ ይበልጥ የሚያተኩሩት ከሰዎች ምቾት ይልቅ በሥራ ውጤት ላይ ነው» የሚል አመለካከት ወጣቱ ሰነዘረ ።

«አይደለም!» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ክርክራቸውን በማጠናከር እንግዳውን አስደነገጡት ። «ይህ ነገር ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ሲባል እሰማለሁ ።» ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ወዲያና ወዲህ መንጐራደድ ጀመሩ ።

«ሰዎች ካልታከሉበት ውጤት እንዴት ስኬታማ ሊሆን ይችላል? ለሰዎችም ለውጤትም እኩል እሰባለሁ ።»

«እስኪ ይችን ተመልከት» አሉት ሥራ አስኪያጁ ለእንግዳው አንዲት መርሕ እያስጨበጡት ። «ሐቁን ቁልጭ አድርጎ እንዲያስታውሰኝ በጠረጴዛዬ ላይ አኖረዋለሁ ።»

ስለ ራሳቸው ደኅንነት የሚሰማቸው ሰዎች ከፍተኛ ምርት ያስገኛሉ ።

ወጣቱ መርሑን እየተመለከተ ሳለ ፣ «እስኪ ስለ ራስህ አስብ ። ምን ጊዜ ነው ተግተህ የምትሠራው? ደኅንነት ሲሰማህ ወይስ ሳይሰማህ?» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ጠየቁት ።

ወጣቱም የሚለውን ካሰላሰለ በኋላ ራሱን በመነቅነቅ ፣ «የበለጠ የማበረክተው ደኅንነት ሲሰማኝ ነው» አላቸው ።



«ልክ ብለሃል ፤ ሌሎችም ሰዎች እንደዚሁ ናቸው» በማለት ሥራ አስኪያጁ ደገፉት ።

ወጣቱ አዲስ ነገር ስለ ተገለጸለት ጠቃሚ ጣቱን ቀሰረ ። «ለካስ ሰዎችን ተግተው እንዲሠሩ ለመርዳት ቁልፉ መርሕ ስለ ራሳቸው ደኅንነት እንዲሰማቸው ማድረግ ነው?»

«አዎን» በማለት ሥራ አስኪያጁም ተስማሙ ።

«ነገር ግን ምርታማነት ሲባል የሥራ ውጤት ብዛት ብቻ አይደለም ። ጥራቱንም እንደሚጨምር ተረዳ» ካሉ በኋላ ወደ መስኮቱ ቀረብ ብለው «እስቲ ወዲህ ና» ፣ አሉት ። በመንገድ ላይ ወደሚሽከረከሩት መኪናዎች እያመለከቱት ፣ «ስንት የባዕድ አገር መኪናዎች እንደሚንቀሳቀሱ ይታይሃል?»

ወጣቱም ቁልቁል ተመልክቶ ፣ «በየቀኑ ብዙዎቹን አያለሁ ። እንደሚመስለኝም እንደነዚህ ዐይነቶች መኪናዎች ቆጣቢና ረጅም ዕድሜ ስለ አላቸው ተጠቃሚዎች አጥብቀው ይፈልጓቸዋል ።»

ሥራ አስኪያጁም ቅር እየተሰኙ ራሳቸውን በመነቅነቅ ፣ «ይሆናል!» አሉት ። «ግን ሰዎች የባዕድ አገር መኪናዎችን ለምን ይገዛሉ በማለት አልተቆረቆርክም? ፋብሪካዎቻችን በቂ መኪናዎች ስለ ማያመርቱ ነው ወይስ ሕዝቡ ከልቡ የሚሻውን ዐይነት ስለማያመርቱለት?» አሉ ሥራ አስኪያጁ ።

«አሁን ገባኝ» ሲል መለሰላቸው ወጣቱ ። «ለካስ ጉዳዩ ብዛትንና ጥራትን ይመለከታል ።»

«እንዴት!» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «ጥራት ሲባልኮ ሕዝቡ የሚፈልገውን ምርት ወይም አገል ግሎት ማበርከት ነው ።»

ሥራ አስኪያጁ መስኮቱ አጠገብ እንደ ቆሙ በሐሳብ ተዋጡ ። በኢንዱስትሪ የበለጸጉት አገሮች ወደኋላ የቀሩትን ለማሳደግ የሚረዳቸውን ቴክኖሎጂ ያበረከቱላቸው በቅርብ ጊዜ መሆኑ ትዝ አላቸው ።

ወጣቱ ሥራ አስኪያጁን ከጥልቅ ሐሳብ ቀሰ ቀሳቸው ። «አንድ ጊዜ በቴሌቪዥን የተመለከትኩት የንግድ ማስታወቂያ ትዝ ይለኛል ። አንድ የውጭ አገር መኪና ስም ያሳዩና በላዩ ላይ የሚከተለው ጽሑፍ ይነበብ ነበር ። በረጅም ጊዜ በሚከፈል ብድር ጥራት ያለውን መኪና በውድ ዋጋ መ ግዛት ከቻልክ ፣ በርካሽ ዋጋ ጥራት የጎደለውን አትግዛ ።»

ሥራ አስኪያጁም ወደ ወጣቱ ዞር ብለው ፣ «የው ይይታችን ጥሩ ማጠቃለያ መሰለኝ ። ዋናው ነጥ ብም ይኸው ነው ። ምርታማነት ብዛትም ጥራትም ነው ።»

እንግዳውና ሥራ አስኪያጁ ወደየመቀመጫ ቸው መመለስ ጀመሩ ። ሥራ አስኪያጁም ፣ «በእር ግጥ እነዚህን ውጤቶች በአመርቂ ሁኔታ ማግኘት የሚቻለው በሰዎች ብቻ ነው» አሉ ።

የወጣቱ የማወቅ ጉጉት እያየለ መጣ ። ቁጭ እንዳለም ይህንን ጥያቄ ሰነዘረ ። «ከዚህ በፊት ተሳ ታፊ ሥራ አስኪያጅ አይደለሁም ብለዋል ። ታዲያ የአመራርዎን ስልት እንዴት ይገልጹታል?»



«በጣም ቀላል ነው ፤ እኔ «የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ነኝ» ሲሉ ያለማመንታት መለሱለት ።

የወጣቱ ፊት በአድናቆት ፈካ ። 'የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ' የሚባል ነገር ከዚያ በፊት ሰምቶ አያውቅም ። «ምንድነኝ አሉ?»

ሥራ አስኪያጁም ሣቅ አሉና ፡ «እኔ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ነኝ ። በዚህ ስያሜ ራሴን የም ጠራበት ምክንያትም በጣም ከፍተኛ ውጤት በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሰዎች ለማግኘት በመቻሌ ነው ።»

ወጣቱ ብዙ ሥራ አስኪያጆችን ቢያነጋግርም ፡ እንደዚህ የሚል አጋጥሞት አያውቅም ። ለማመን ያዳግታል ። የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ ጥሩን ውጤት የሚያስገኝ !?

ጥርጣሬውን ከፊቱ ላይ በማንበብ ፡ ሥራ አስ ኪያጁ ፣ «የምነግርህን ተጠራጥረሃል ፡ አይደለም? ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ መሆኔን አላመንክም» አሉት ።

«እንደ ዕውነቱ ከሆነ እንደዚህ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ ለማሰብ ያዳግተኛል» ሲል ወጣቱ መለሰላቸው ።

ሥራ አስኪያጁ አሁንም ሣቅ አሉና ፣ «አዳም ጠኝ ፣ በእርግጥ ምን ዐይነት ሥራ አስኪያጅ እን ደሆንኩ ለማወቅ ከፈለግህ ሰዎቼን ማነጋገሩ ይበ ጅሃል ።»

ሥራ አስኪያጁም ወደጐን ደገፍ ብለው በልዩ መገናኛ ጸሐፊያቸውን አነጋገሯት ። ጸሐፊዋም ፣ ወይዘሮ ሜትካል ፍ ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ብቅ ብላ ለወጣቱ አንድ ገጽ ጽሑፍ ሰጠችው ።

«በወረቀቱ ላይ የምታነበው ለእኔ ተጠሪ የሆኑትን የስድስት ሰዎች ስም ዝርዝር ፣ የሥራ መደብና የስልክ ቁጥር ነው» ሲሉ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ገለጹለት ።

«ማንኛቸውን ባነጋግር ይሻላል?» በማለት ወጣቱ ጠየቃቸው ።

«ያ የራስህ ምርጫ ነው» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ መለሱለት ። «ያሰኘህን ስም ምረጥ ። አንደኛቸውን ወይንም ሁሉንም አነጋግራቸው ።»

«ደህና ፣ በማን ልጀምር ማለቴ ነው?»

«ቀደም ብዬ ነግሬሃለሁ ። ለሌሎች ሰዎች ውሳኔ አልሰጥም» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ተከሳተሩ ። «ራስህ ወስን ።» ብድግ ብለው እንግዳውን ወደ በሩ መሩት ።

«ከእንዴም ሁለቴ ቀላል ነገር እንድወስንልህ ጠይቀኸኛል ። እውነቱን ልንገርህ ፣ እንዲህ ያለ ነገር ያናድደኛል ። የተናገርኩትን እንድደጋግም አታድርገኝ ። አንድ ስም ምረጥና ለማወቅ የፈለግከውን ጠይቅ ፤ አለበለዚያ ስለ ውጤታማ ሥራ አመራር ለመረዳት የጀመርከውን ፍለጋ ሌላ ቦታ ቀጥል ።»



እንግዳው ተደናግጠ መናገር አቃተው ። በጣም ጭንቀት ተሰማው ። ለአፍታ ያህል የሰፈነው ጸጥታ በጣም ረዘመ ።

ከዚያ በኋላ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ወጣቱን ትኩር ብለው ዐይን ዐይኑን ተመለከቱና ፣ «ኃላፊዎች ሰዎችን እንዴት እንደሚመሩ ለማወቅ ትፈልጋለህ ፣ እናም በዚህ አደንቅሃለሁ» በማለት ጨበጡት ።

«ከሰዎቼ አንዳንዶቹን ካነጋገርክ በኋላ ፣ ምንም ዐይነት ጥያቄ ቢኖርህ ፣ እንደገና ብቅ በል ። ስለ አመራር ለመማር ያለህን ዝንባሌና ጉጉት ከፍተኛ ግምት እሰጠዋለሁ ። እንዲያውም ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅን ፅንሰ ሐሳብ እንደ ስጦታ ላበረክትልህ እወዳለሁ ። ለእኔም አንድ ሰው በአንድ ወቅት አበርክተውልኝ ፣ አሁን በሥራዬ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስገኝቶልኛል ። ፅንሰ ሐሳቡን በሚገባ እንድትረዳው እፈልጋለሁ ። ካስደሰተህ ፣ ማን ያውቃል ፣ አንተው ራስህ አንድ ቀን የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ትሆን ይሆናል» ብለወ አሰናበቱት ።

«አመሰግናለሁ» አለ ወጣቱ ።

ከሥራ አስኪያጁ ቢሮ እንደ መደነጋገር ብሎት ወጣ ። በጸሐፊዋ ቢሮ ውስጥ በማለፍ ላይ እንዳለ «ከፊትህ ላይ እንደማነብበው የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጃችንን ማንነት የተገነዘብክ ትመስላለህ» አለችው ጸሐፊዋ ከሁኔታው በመረዳት ።

ወጣቱም ለዘብ ባለ ድምፅ ፡ ነገሮችን እያገናዘበ ፡ «ማንነታቸውን ለማስተዋል የቻልኩ መሰለኝ» ሲል መለሰላት ።

ወይዘሮ ሜትካልፍም ፡ «ከፈለግህ ልረዳህ እችላለሁ ። ለርሳቸው ተጠሪ የሆኑትን ስድስቱን ሰዎች በስልክ አነጋግሬያቸዋለሁ ። አምስቱ እዚሁ አሉ ፡ ሁሉም ሊያነጋግሩህ ፈቅደዋል ። ካነጋገርካቸው በኋላ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጃችንን ምንነት በበለጠ መረዳት ትችል ይሆናል» አለችው ።

ወጣቱም ጸሐፊዋ ላደረገችለት እርዳታ አመሰገናት ። ያቀረበችለትን ዝርዝር ተመልክቶ ሦስቱን አቶ ትሪኔልን ፡ አቶ ሌቪንና ወ/ሮ ብራውንን ለማነጋገር ወሰነ ።



## የመጀመሪያው ምሥጢር

### የአንድ ደቂቃ ግቦች

ወጣቱም አቶ ትሪኔል ቢሮ እንደ ደረሰ ፡ መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሰው በፈገግታ ተቀበለው ።

«ሽማግሌውን አነጋግረህ ነበር ። ልዩ ሰው ናቸው ፡ አይደል?» አለው አቶ ትሪኔል ።

«ይመስላሉ» ሲል ወጣቱ መለሰ ።

«ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ መሆን ምን እንደሆነ ነግረውሃል?» በማለት አቶ ትሪኔል ጠየቀው ።

«በእርግጥ ነግረውኛል ፤ የእውነት አይደለም ፡ ነው እንዴ?» ሲል ወጣቱ ጥርጣሬውን ገለጸ ።

«ባትጠራጠር ይሻላል ። እኔና እርሳቸው እንኳ እምብዛም አንገናኝም ።»

«ምንም ዐይነት እርዳታ ከርሳቸው አላገኝም ነው የሚሉኝ?» ሲል ግራ የተጋባው ወጣት ጠየቀው ።

«በጣም አነስተኛ ነው ፣ ይሁን እንጂ አዲስ ሥራ ስጀምር ወይም ኃላፊነት ሲሰጠኝ የተወሰነ ጊዜ ከእኔ ጋር ያሳልፉሉ ። ይኸውም ያንድ ደቂቃ ግብ በሚቀይሱበት ጊዜ ነው ።»

«ያንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ፣ ምን ማለት ነው?» አለ ወጣቱ። «ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅነታቸውን እንጂ ፣ ስለ አንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ምንም የነገሩኝ ነገር የለም ።»

«ይህ ከአንድ ደቂቃ የሥራ አመራር ሦስቱ ምሥጢሮች የመጀመሪያው ነው» ሲል ትሪኔል መለሰለት ።

«ሦስት ምሥጢሮች!» አለ ወጣቱ ይበልጥ ለማወቅ እየጓጓ ።

«አዎን» አለ ትሪኔል ፣ «የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ለአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር መሠረትና የመጀመሪያው ምሥጢር ነው ። በብዙ ድርጅቶች ውስጥ ሠራተኞችን ምን እንደሚሠሩ ብትጠይቃቸውና ያንኑ ጥያቄ ለአለቃቸው ብታቀርብ ብዙ ጊዜ ሁለት የተለያዩ የሥራ ዝርዝሮች ታገኛለህ ። እንዲያውም ፣ ከዚህ በፊት በሠራሁባቸው ጥቂት ድርጅቶች ፣ የሥራ ኃላፊነቴ ነው በምለው እና የቅርብ አለቃዬ ደግሞ እንደ ኃላፊነቴ በሚቆጥራቸው ተግባራት መካከል ተዛምዶ ቢኖር የአጋጣሚ ነው ። በዚህ የተነሣ ሥራዬ መሆኑን እንኳን የማላውቀውን ነገር አላከናወንክም እየተባልኩ ችግር ይደርስብኝ ነበር ።»



«የዚህ ዐይነት ችግር በዚህ ድርጅት ውስጥ ተፈጥሮ ያውቃል?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ።

«አይ» አለው ትሪኔል ። «እዚህ እንዲህ ያለ ነገር ጭራሽ የለም ። የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ኃላፊነታችንና ተጠያቂ የምንሆንባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ሁልጊዜ ይገልጹልናል ።»

«እንዳው እንዴት ነው ይህን የሚገልጹላችሁ?» ወጣቱ ለማወቅ ፈለገ ።

«በሚገባ ነዋ!» በማለት በፈገግታ ወደእርሱ ዞሮ ማስረዳቱን ጀመረ ። «ምን መሥራት እንደ ሚገባኝ አንድ ጊዜ ከነገሩኝ ፣ ወይንም ምን መሥራት እንዳለበት ከተስማማን ፣ እያንዳንዱ የሥራ ግብ ካንድ ገጽ ባልበለጠ ወረቀት ላይ ይመዘገባል ። ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ፣ የሥራውን ግብና የአፈጻጸም መለኪያውን ከ250 በማይበልጡ ቃላት መግለጽ ይቻላል ብለው ያምናሉ ። ያንን ጽሑፍ ማንም ሰው በአንድ ደቂቃ ውስጥ ማንበብ መቻል እንዳለበት አበክረው ይናገራሉ ። እርሳቸው አንድ ቅጅ ሲይዙ ሌላውን እኔ እይዛለሁ ። ስለዚህ ሁሉ ነገር ግልጽ ነው ። በመሆኑም ሁለታችንም የሥራውን እርምጃ በየተወሰነ ጊዜ መከታተል እንችላለን ።»

«እነዚህን የአንዳንድ ገጽ ሰነዶች ለሁሉም ግብ ትጠቀሙባቸዋላችሁ?» ሲል ወጣቱ ጠየቀው ።

«አዎን» በማለት ትሪኔል መለሰ ።

«እነዚህ የአንዳንድ ገጽ ጽሑፎች ለእያንዳንዱ ሰው ከታደሉ በርካታ አይሆኑም?»

«በፍጹም» ሲል ትሪኔል መለሰለት ። «ሽማግሌው «80—20» በተሰኘ የግብ ቅየሳ ሕግ ያምናሉ ። ይህም ማለት ከዋነኞቹ ውጤቶችህ 80% የሚሆኑት ከ20% ግብህ ይመነጫሉ ። በመሆኑም የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳን በ20% እናሰላዋለን ። ማለትም ከሥራ ኃላፊነታችን አንጻር ወሳኝ የሆኑትን ተግባራት በጠቅላላው ምናልባት ከ3—6 በሚደርሱ ግቦች እናጠናቅቃለን ። እርግጥ ነው ፣ አዲስ ፕሮጀክት በተፈጠረ ቁጥር ለዚያ የሚሆን የተለየ የአንድ ደቂቃ ግብ እናዘጋጃለን ።»

«ይደንቃል» ሲል ወጣቱ አስተያየቱን ሰጠ ። «የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ምን እንደሆነ የተረዳሁ ይመስለኛል ። በጣም ግልጽ የሆነ የአመራር ፍልስፍና ነው ፤ ገና ተግባሩን ሲጀምር እያንዳንዱ ሰው ምን እንደሚጠበቅበት ያውቃል ።»

«ትክክል ነው» ሲል ትሪኔል ተስማማ ።

«ስለዚህ ያንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ኃላፊነትን ከሥራ አፈጻጸም ጋር ያቀናጃል ማለት ነው?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ።

«አይደለም ። የተግባራችንን ምንነት ካወቅን በኋላ ፣ ሥራ አስኪያጁ ውጤታማ የሥራ አፈጻጸም ምን እንደሆነ መረዳታችንን ለማረጋገጥ ይሞክራሉ ። በሌላ አነጋገር ፣ የሥራ አፈጻጸም ደረጃዎችን ግልጽ ያደርጉልናል ። ከእያንዳንዳችን ምን እንደሚጠበቅ ያሳዩናል ።»



«ከእናንተ ምን እንደሚጠብቁ እንዴት ያሳዩዋችኋል?» ሲል ወጣቱ ጠየቀው ።

«በምሳሌ ላብራራልህ» አለ ትሪኔል ።

«ለአንድ ደቂቃ የሥራ ግቦቼ መሳካት አንዱ መመሪያ «የአፈጻጸምን ችግሮች ከለየህ በኋላ መፍትሔ አግኝተህላቸው በተግባር ላይ ማዋል ሁኔታ ታውን ፊት ከነበረበት ሙሉ በሙሉ ይቀይሩታል» የሚል ነበር ።

«እዚህ መሥሪያ ቤት ሥራ እንደ ጀመርኩ አንድ መፈታት ያለበት ችግር አጋጠመኝ ፤ ግን ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝ አላወቅሁም ። ስለዚህ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁን ባስልክ አነጋገርኳቸው ። ስልኩን እንዳነሡ ፣ 'አንድ የሥራ ችግር አጋጠመኝ' አልኳቸው ። ሌላ ቃል ከመተንፈሴ በፊት ፣ ጥሩ !...... የተቀጠርከው የዚህን ዐይነት ችግር ለመፍታት ነው ብለውኝ ድምጻቸውን አጠፉ ። የማደርገው ነገር ግራ ገባኝ ። ጸጥታው አስደነገጠኝ ። እየተንተባተብኩ ፣ 'ይህንን ችግር እንዴት እንደምፈታው አላወቅኩም' አልኩ ።

«ትሪኔል ፣ ለወደፊት ከግቦችህ አንዱ የሥራህን ችግሮች ለይተህ ማወቅና መፍትሔአቸውን መፈለግ ነው ። አሁን ግን አዲስ ስለሆንክ ቢሮዬ ድረስ ናና እንነጋገርበት' አሉኝ ።

«ቢሮዋቸው እንደ ደረስኩ ፣ 'ትሪኔል ፣ ችግርህን እስቲ ንገረኝ ። እንዴት እንዳስቸገረህ ነው የምታብራራልኝ' አሉኝ ።

«እንዴት እንዳስቸገረህ ሲሉኝ ‘ምን ማለትዎ ነውገ’ ብዬ ጠየኳቸው ።

«ሥራ አስኪያጁም ‘አስተያየትህን ወይም ስሜትህን ብቻ ልሰማ አልፈልግም ፤ አጋጠመኝ የምትለውን ችግር ማየትና መመዘን በሚያስችል መንገድ ግለጽልኝ’ አሉኝ ።

«የተቻለኝን ያህል እርሳቸው በጠየቁኝ መንገድ ችግሩን ለማስረዳት ሞከርኩ ።

«ትሪኔል ፣ ጥሩ ነው! አሁን ምን እንዲሆንልህ እንደምትፈልግ ችግሩን ካስከተለብህ ድርጊት አንጻር ግለጽልኝ’ አሉኝ ።

«አልገባኝም’ አልኳቸው ።

«እንግዲያውስ ‘ጊዜዬን አታባክን’ አሉኝ ቆጣ ብለው ።

«እነጋገራቸው አስገርሞኝ ለጥቂት ሴኮንዶች ጸጥ አልኩ ። ምን እንደማደርግ ጨነቀኝ ፤ ምስጋና ይግባቸውና ፣ ራሳቸው የሠፈነውን ጸጥታ ገፈፉልኝ ።

«ምን እንዲሆንልህ እንደምትፈልግ ልታስረዳኝ ካልቻልክ ፣ ገና ችግር አላጋጠመህም ማለት ነው ። እንዲያው ነው ኑቤቱታ የምታሰማ ። ‘ችግር አለ የሚባለው አጋጠመኝ በምትለውና እንዲሆን በምትፈልገው ነገር መካከል ግጭት ያለ እንዲሆን ብቻ ነው ።’



«ነገር ቶሎ የሚገባው ሰው እንደ መሆኔ ፣ ምን እንዲሆንልኝ እንደምፈልግ በፍጥነት ተገነዘብኩ ። ከነገርኳቸው በኋላም አሁን ባለው ችግርና እንዲሆንልኝ በምፈልገው መካከል ያለውን ልዩነት ምን እንደ ፈጠረው እንዳብራራላቸው ጠየቁኝ ።

«ከዚያ በኋላ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ፣ ‹ደህና ፣ ከእንግዲህ ምን ታደርጋለህ?’ አሉኝ ።

«ጥሩ፣ ‘ተራ ቁ. (ሀ)ን ተግባራዊ አደርጋለሁ’ አልኩ ።

«‘(ሀ)ን ብትፈጽም እንዲሆን የምትፈልገው ነገር በእርግጥ ተግባራዊ ይሆንልሃል?’ ብለው ጠየቁኝ ።

«‘አይሆንም’ አልኳቸው ።

«‘እንግዲያውስ መፍትሔህ አይረባም ። ሌላስ ምን ማድረግ ትችላለህ?’ ብለው ጠየቁኝ ።

«‘(ለ)ን ማድረግ እችላለሁ» አልኳቸው ።

«‘(ለ)ን ብታደርግ እንዲሆን የምትፈልገው በትክክል ሊሆን ይችላል?’ ሲሉ እንደገና መልሰው ጠየቁኝ ።

«‘አይሆንም’ አልኳቸው ።

«‘እንግዳውስ ይህም መፍትሔህ ዋጋቢስ ነው ። ሌላ ለማድረግ የምትችለው ነገር አለ?’ አሉኝ ።

«ለሁለት ደቂቃዎች ያህል አሰላስልኩና (መ)ን ማድረግ እንደምችል ነገርኳቸው ። ነገር ግን (መ)ንም ባደርግ የምፈልገውን ውጤት አላገኝም ። ‘ስለዚህ

ይህም ፋይዳቢስ መፍትሔ ነው ፡ አይመስልዎትም?’ አልኩ ።

«‘ያልከው ትክክል ነው ። አሁን ነገሩ እየገባህ መጥቷል’ አሉኝ ፈገግ ብለው ። ‘ሌላ ማድረግ የምትችለው ነገር አለ?’ ብለው ጠየቁኝ ።

«‘ምናልባት በተናጠል ካቀረብኳቸው መፍትሔዎች አንዳንዶቹን ለማጣመር እሞክራለሁ’ አልኳቸው ።

«‘መሞከር የሚገባው ተግባር ይመስላል’ አሉኝ ።

«‘እንዲያውም (ሀ)ን በዚህ ሳምንት ፡ (ለ)ን በሚቀጥለው ፡ (መ)ን ደግሞ በተከታዩ ሳምንት ባከናውን ችግሬ ተቃለለልኝ ማለት ነው ። ግሩም ነው! በጣም አመሰግንዎታለሁ ። ችግሬን ፈቱልኝ’ አልኩ ።

«በጣም ተቆጡ ። ‘አልፈታሁልህም ፡ አንተው ራስህ ነህ መፍትሔውን ያገኘኸው’ አሉኝ ። «ጥያቄዎች አቀረብኩልህ — አንተው በራስህ ለራስህ የምታነሣቸው ጥያቄዎች ። አሁን ውጣልኝና ላጋጠሙህ ችግሮች በእኔ ሳይሆን በራስህ የሥራ ጊዜ መፍትሔያቸውን ፈልግ ።’

«በእርግጥ ፡ አስተዋጽኦዋቸው ምን እንደሆነ ይገባኛል ። ለወደፊት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በግሌ መፍታት የምችልበትን መንገድ አሳይተውኛል ።



«ከዚያም በመቀመጫቸው ብድግ ብለው አተኩረው ዐይን ዐይኔን እየተመለከቱ፡ (ትሬኔል ፡ ጐበዝ ሰው ነው ።»ለወደፊት ችግር ቢያጋጥምህ ይህን አስታውስ) አሉኝ ።

«ከቢሮዋቸው በፈገግታ ወጥቼ መሔዴ ትዝ ይለኛል» አለ ።

አቶ ትሬኔል ከመቀመጫው ላይ ወደ ኋላው ተለጠጠና ያችን ወቅት ልክ ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተገናኘባት ቀን አድርጎ ተመለከታት ።

«አሃ!» በማለት ወጣቱ የሰማውን በሐሳቡ ያወጣ ያወርድ ጀመር ።

## የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ሲጠቃለል

1. በግቦችህ ተማመን ፤
2. ውጤታማ ተግባር ምን እንደሚመስል አስተውል ፤
3. እያንዳንዱን ግብህን ከ250 ባነሱ ቃላት ባንድ ገጽ ላይ አስፍር ፤
4. ከአንድ ደቂቃ በላይ አይወስድብህምና ፣ እያንዳንዱን ግብህን ደግመህ ደጋግመህ አንብብ ፤
5. አልፎ አልፎ በቀን ላንድ ደቂቃ ያህል የአፈጻጸምህን ሁኔታ አጢን ፤
6. ከንውንህ ከግብህ ጋር መጣጣሙን ወይም አለመጣጣሙን አገናዝብ ።

«ይኸው ነው ፤ የምነግርህን በፍጥነት መረዳት የምትችል ሰው ነህ» አለው ትሪኔል ።

«አመሰግናለሁ» አለ ወጣቱ ፣ በሙገሳው እየተደሰተ ። «ወደፊት ለማስታወስ ስለምፈልግ ፣ አሁን የነገሩኝን በማስታወሻዬ ልመዝግብ» ብሎ አዘውትሮ በሚይዘው ሰማያዊ ማስታወሻ ደብተሩ ባጭር ባጭሩ የፈለገውን ከመዘገበ በኋላ ፣ ወደፊቱ ዘምበል በማለት «የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ፣



የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ከሚያበቁት ሦስት ምሥጢሮች የመጀመሪያው ከሆነ የቀሩት ሁለቱ ምንድን ናቸው?» ሲል ጠየቀ ።

ትሪኔልም ፈገግ ብሎ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ «ይህንን ነገር ለምን ሌቪንን አትጠይቀውም? ዛሬ ጥዋት እርሱንም ለማነጋገር ቀጠሮ ተይዞልሃል ፣ አይደለም?» አለው ።

ወጣቱም ተገረመ ። ትሪኔል ይህንን እንዴት ማወቅ ቻለ? «አዎን ፣ ቀጠሮ ተይዞልኛል ። የሥራ ጊዜዎን በማጥፋት ላደረጉልኝ ገለጻ በጣም አመሰግናለሁ» በማለት ለመሔድ ብድግ ብሎ ትሪኔልን ጨበጠው ።

ትሪኔልም «ምንም አይደለም ፤ ባሁኑ ወቅት በብዛት አሉኝ ከምላቸው ነገሮች አንዱ ጊዜ ነው ። ምናልባትም ሳትገነዘብልኝ አትቀርም ፣ እኔ ራሴምኮ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ እየሆንኩ ነኝ ።»

## ሁለተኛው ምሥጢር

### የአንድ ደቂቃ ሙገሳ

ወጣቱ ከትሬኔል ቢሮ ወጥቶ ሲሔድ የሰማው ነገር ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ተገረመ ። ገሃድ የሆነ ቁም ነገር ነው።«እያንዳንዱ ሠራተኛ የተግባሩን ምንነት መገንዘቡን ካላረጋገጠ አንድ ሰው እንዴት ምስጉን ሥራ አስኪያጅ ሊሆን ይችላል? ቀልጣፋነቱስ በምን ይታወቃል?»

ወጣቱም እስከ ሕንፃው መጨረሻ ተጓዘና ወደ ሁለተኛው ፎቅ ለመውጣት በሊፍት ተሳፈረ ። አቶ ሌቪ ቢሮም እንደ ደረሰ ፡ በጣም ወጣት የሆነ ሰው በማግኘቱ ተደነቀ ። ሌቪ ዕድሜው ምናልባት ወደ 20 መጨረሻ ወይም 30 ዓመት መጀመሪያ ቢሆን ነው ። «ታዲያስ»? 'ሽማግሌውን' አነጋገርካቸው? የተለዩ ሰው ናቸው ፤ አይደሉም?» አለው ።

ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ «የተለየ ሰው» እየተባለ መጠራቱን ወጣቱ ተለማምዶታል ።

«የተለዩ ሰው አድርጌ ነው የገመትኳቸው» ሲል ወጣቱ መለሰ ።

«የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ስለ መሆን ኢሚወቱህ ሲል ጠየቀው?» ሌቪ ።



«በእርግጥ ነግረውኛል ። ግን ሊሆን የሚችል አይመስልም ፤ ይመስላል?» ትሬኔል ከነገረው ሌላ የተለየ መልስ ይገኝ እንደሆን በማለት ወጣቱ ጠየቀ ።

«እርግጠኛነቱን ማመኑ ይበጃል ። እኔ እንኳ እምብዛም አልቀርባቸውም ።»

«ምንም ዐይነት እርዳታ ከርሳቸው አላገኝም ነው የምትለኝ?» ብሎ ወጣቱ ጠየቀው ።

«አዲስ ሥራ ስጀምር ወይም ኃላፊነት ሲሰጠኝ መጠነኛ ጊዜ ከእኔ ጋር ቢያሳልፉም ፤በእውነቱ ከእርሳቸው የማገኘው ርዳታ በጣም አነስተኛ ነው ።»

«ቀደም ብዬ ስለ አንድ ደቂቃ የግብ ቅየሳ ምንነት ተገንዝቤያለሁ» ሲል ወጣቱ ጣልቃ ገባ ።

«እኔን እንኳ የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ይህን ያህል አያሳስበኝም ። ልጠቅስልህ የምፈልገው ስለ አንድ ደቂቃ ሙገሳ ነው» አለ ሌቪ ።

«የአንድ ደቂቃ ሙገሳ!» በማለት አስተጋባ ወጣቱ ። «የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ሁለተኛው ምስጢር መሆኑ ነው?»

«እንዴታ!» በማለት መለሰ ሌቪ ። «እንዲያውም ገና ሥራ እንደ ጀመርኩ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ አስጠርተውኝ ገለጻ ያደረጉልኝ ስለዚሁ ጉዳይ ነው ።»

«ምን ነበር?» ሲል እንግዳው ጠየቀው ።

«ስለ ሥራዬ ክንውን ቁልጭ ያለ ግምገማ
ከሰጡኝ በኋላ ወደፊት በትጋት ለመሥራት በጣም
ቀላል እንደሚሆንልኝ ነገሩኝ ። ከፍ ያለ ደረጃ
እንደምደርስና ተግባሬንም እንደማፈቅር ምኞታ
ቸውን ገለጹልኝ ። በማያሻሙ ቃላትም የሥራ አፈ
ጻጸሜ መቼ ጠንካራ ፣ መቼ ደግሞ ደካማ እንደሚሆን
ለመጠቆም እንደሚሞክሩ ነገሩኝ ። ከዚያም በመ
ጀመሪያው ወቅት ሁለታችንንም ሳያስደስት እንደ
ሚችል አስጠንቀቁኝ ።»

«ለምን?» ሲል እንግዳው ጠየቀ ።

«ምክንያቱም ፣ በዚያን ጊዜ እንደ ገለጹልኝ ፣
አብዛኞች ሥራ አስኪያጆች በዚህ ዘዴ ስለማይመ
ሩና ሠራተኞችም ስለ አልለመዱት ነው ። ይሁን
እንጂ ፣ የዚህ ዐይነት ግምገማ ብዙ ሊረዳኝ እንደ
ሚችል አረጋገጡልኝ ።

«ስለምትናገረው አንድ ምሳሌ ልትሰጠኝ ትች
ላለህ?» ሲል ወጣቱ ጠየቀው ።

«በሚገባ» አለ ሌቪ ። «መሥራት ከጀመርኩ
በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ አስኪያጁ ጋር የአንድ
ደቂቃ ግብ አብረን ከቀየስን በኋላ ፣ በቅርብ እንደ
ሚከታተሉኝ አስተዋልኩ ።»

«'በቅርብ ይከታተሉኛል' ስትል ምን ማለ
ትህ ነው?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ።



«በሁለት መንገዶች ነበር ክትትል የሚያደ
ርጉብኝ» በማለት ሌቪ አስረዳው ። «በአንደኛ
ደረጃ ፣ ተግባራቴን በትኩረት ይመለከታሉ ። ከአ
ጠገቤ ፈጽሞ አይርቁም ። ሁለተኛ ስለ ሥራዬ አር
ምጃ የማጠናቅረውን ዝርዝር ማስታወሻ በየጊዜው
እንድልክላቸው ያስጠንቅቁኝ ነበሩ ።»

«ግን ይህንን ለምን ያደርጋሉ?» በማለት ወጣቱ
ጠየቀ ።

«በመጀመሪያ ሰሞን ስለ አላመኑኝ ስለላ የሚ
ያካሒዱብኝ መስሎኝ ነበር ፣ ይህንን ለምን እንደማያ
ደርጉ ለእርሳቸው ተጠሪ ከሆኑት ከጥቂት ሌሎች
ሰዎች እስከረዳ ።»

«ምን አሉህ?» ወጣቱ ለማወቅ ፈለገ ።

«አንድ ነገር በትክክል መሥራቴን ለማረጋ
ገጥ መሞከራቸው ነበር» አለ ሌቪ ።

«አንድ ነገር በትክክል መሥራትህን ሊያረጋ
ግጡ» በማለት አስተጋባ ወጣቱ ።

«አዎን» ሲል መለሰለት ሌቪ ። «እንዲያውም
እዚህ አካባቢ እንዲህ የሚል መርሕ አለ ።

«ሰዎች የመጨረሻ ችሎታቸውን እንዲያሳዩ አበረ
ታታቸው ። አንድን ነገር በትክክል ሲሠሩ አግኛ
ቸው ።»

ሌቪ ንግግሩን በመቀጠል ፡ «በብዙ ድርጅቶች ውስጥ ሥራ አስኪያጆቹ አብዛኛው ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ሰዎቻቸው ምን ሲሠሩ ለማግኘት ይመስልሃል?» በማለት ወጣቱን ጠየቀው ።

ወጣቱም ፈገግ አለና የሚጠበቀውን መልስ በመገመት ፡ «ስሕተት ሲሠሩ ለማግኘት ነው» አለ ።

«ትክክል!» አለ ሌቪ ። «እዚህ ግን የምናጐላው በጐውን አስተዋጽኦዋቸውን ነው ። ሰዎቻችን አብዛኛውን ጊዜ ተግባሮቻቸውን በትክክል ሲያከናውኑ እናገኛቸዋለን ።»

ወጣቱም በማስታወሻው ደብተሩ ጥቂት ነጥቦችን ካሰፈረ በኋላ ፡ ጥያቄ አቀረበለት ። «አቶ ሌቪ ፡ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ አንድ ነገር በትክክል ስትሠራ ቢያገኙህ ምን ያደርጉልሃል?»

«የአንድ ደቂቃ ሙገሳ የሚያበረክቱልህ በዚያን ጊዜ ነው» ሲል ሌቪ በፈገግታ መለሰለት ።

«'ያንድ ደቂቃ ሙገሳ' ስትል ምን ማለትህ ነው?» ሲል ወጣቱ የበለጠ ለመረዳት ጠየቀው ።

«ደኅና ፡ አንድ ነገር ትክክል ስትሠራ ካዩህ ይቀርቡሃል ። ይኸውም ብዙውን ጊዜ ትከሻህን በመያዝ ወይም ለጥቂት ደቂቃዎች በወዳጅነት መንፈስ ተጠግተውህ በማነጋገር ሊሆን ይችላል ።»

«ተጠግተውህ ሰውነትህን ሲነኩህ ጭንቀት አይሰማህም?» ብሎ ወጣቱ በመገረም ጠየቀው ።



«እንዲያውም!» አለ ሌቪ ፡ «ባይገርምህ ያበረታታኛል ። እንደሚያስቡልኝና በሥራዬ እንዳደግ እንደሚፈልጉ ይሰማኛል ። ትከሻዬን መታ መታ የሚያደርጉኝ ለትንሽ ጊዜ ነው ፤ ነገር ግን የሚደግፉኝ መሆናቸውን ከልብ ያስገነዝበኛል ።»

«ከዚያ በኋላም ዐይን ዐይንህን ትኩር ብለው ይመለከቱና ምን ነገር ትክክል እንደ ሠራህ ግልጽ አድርገው ይነግሩሃል ። ወዲያውም የደስታህ ተካፋይ መሆናቸውን ያበሥሩሃል ።»

«እንደዚህ የሚያደርግ ሥራ አስኪያጅ መናሩን ከቶውም የሰማሁ አይመስለኝም» ሲል ጣልቃ ገባ ወጣቱ ። «እንዲያ ማድረጋቸው ሳያስደስትህ አይቀርም ።»

«በጣም እንጂ! በጣም ያስደስተኛል» በማለት ሌቪ አረጋገጠለት ። «በአንደኛ ደረጃ ፡ ሙገሳውን የማገኘው ወዲያውኑ ነው ። «ፈገግ ብሎ ወደ እንግዳው ዘምበል አለ ። ከዚያም ሣቀና «ምን ማለቴ እንደሆን የሚገባህ ከሆነ ፡ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ግምገማን መጠበቅ የለብኝም ።» ሁለቱም ሰዎች ፈገግ አሉ ።

«በሁለተኛ ደረጃ ፡ ትክክል የሠራሁት ነገር ምን እንደሆነ ግልጽ አድርገው ስለሚጠቁሙኝ በሐቀኝነት መንፈስ ድካሜን እንደ መዘኑልኝ ይገባኛል ። በሦስተኛ ደረጃ ፡ አለማወላወላቸው ያስደስተኛል።»

«መወላወል አያውቁም?» ኦስተጋባ ጠጣቱ ፡ የበለጠ ለማወቅ ብሎ ።

«አዎን» አለ ሌቪ ። «ሥራዬን በደህና በማከና
ወኔ ሙገሳ የሚገባኝ ከሆነ ፣ ከሌላ ዘንዳ ችግር
ቢያጋጥማቸውም ፤ ለእኔ የሚገባኝን ሙገሳ አይነ
ፍጉኝም ። ምናልባት በሌሎች ነገሮች ቢናደዱ እንኳ
የእኔን ሁኔታ የሚመለከቱት በጊዜው ሌላ ቦታ ካጋ
ጠማቸው ጉዳይ ለይተው ነው ። እና ይህንን ሚዛና
ዊነታቸውን ከልቤ አደንቅላቸዋለሁ ።»

«ይህ የሙገሳ ጋጋታ የሥራ አስኪያጁን ጊዜ
እያባከንባቸውም?» በማለት ወጣቱ ጠየቀው ።

«ኧረ በጭራሽ» አለ ሌቪ ። «ልብ በል ፣
ሰዎች እንዳስተዋልካቸውና እንደምታስብላቸው እን
ዲያውቁ ለማድረግ ለረጅም ጊዜ ማሞጋገስ የለብ
ህም ። አብዛኛውን ጊዜ ሙገሳው ‘አንድ ደቂቃም’
አይሞላ ።

«ለካስ ስለዚህ ነው የአንድ ደቂቃ ሙገሳ የተ
ባለው!» አለ እንግዳው፣ በማስታወሻው ላይ የመዘ
ገበውን ትምህርት እያጣጣመ ።

«ትክክል» ሲል ሌቪ መለሰለት ።

«ትክክለኛ ነገር በመሥራት ላይ ሳለህ ሊያ
ገኙህ የሚሞክሩት አዘውትረው ነው?» በማለት
ወጣቱ ጠየቀው ።

«አይ! እንዲያስ አይደለም» አለው ሌቪ ።
«ይህንን የሚያደርጉት ገና እዚህ ሥራ ስትጀምር ፣
ወይም አዲስ ፕሮጀክት ስትቀይስ ፣ ወይም አዲስ
ኃላፊነት ስትረከብ ነው ። ከሥራህ ጋር በሚገባ
ከተዋወቅህ በኋላ ግን፣በአመዛኙ በአካባቢህ አይታ
ዩም ።»



«ለምን?» በመገረም ጠየቀ ወጣቱ ።

«ምክንያቱም ሥራህ ለሙገሳ የሚያበቃ መሆ
ኑን እርሳቸውና አንተ ልታውቅ የምትችሉበት
ሌሎች መንገዶች አሉ ። ሁለታችሁም ለድርጅቱ የመ
ረጃ ማጠናቀሪያ ሥርዓት ውስጥ የሰፈሩትን ነጥቦች
ለምሳሌ የሺያጭ መጠን ፣ ወጭዎች ፣ የምርት ፕሮ
ግራም የመሳሰሉትን ማየት ትችላላችሁ ። ከዚያም»
ሲል ሌቪ ቀጠለ ፣ «ከጊዜ በኋላ አንተው ራስህ በት
ክክል ይህንን ልምድ በተግባር ላይ ማዋልህን ታው
ቅና ራስህን በራስህ ማሞገስ ትጀምራለህ ። ደግሞ ፣
መቼ እንደገና እንደሚያሞግሱህ ስለማታውቅ ሁል
ጊዜ በተጠንቀቅ ትገኛለህ ። ይህም እርሳቸው ባካ
ባቢህ ባይኖሩም፣ከመሥራት እንዳትቦዝን ያደርግ
ሃል ። ብልጣ ብልጥነት አይደለም ። በሕይወቴ እን
ደዚህ በትጋት የሠራሁበት ቦታ የለም ።»

«ይህ በእውነቱ የሚገርም ነው» በማለት አስ
ተያየቱን ሰጠ ወጣቱ ። «ስለዚህ የአንድ ደቂቃ
ሙገሳ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ሌላው
ምስጢር ነው ።

«ነው እንጂ ፣ በሚገባ» አለ ሌቪ ዐይኑን እያ
ቁለጨለጨ ። አንድ ሰው የአንድ ደቂቃ ሥራ አመ
ራር ምሥጢሮችን ሲማር መመልከቱ አስደሰተው ።

እንግዳውም ማስታወሻውን እየተመለከተ ፣
ስለ አንደ ደቂቃ ሙገሳ ምን ምን እንደ ተማረ በፍጥ
ነት ከለሰ ።

## ያንድ ደቂቃ ሙገሳ ሲጠቃለል

የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ጥሩ ውጤት የሚያስገኘው፡

1. ከመጀመሪያው ፡ ለሠራተኞችህ ስለ ሥራቸው አፈጻጸም እንደምታስታውቃቸው ንገራቸው ፤
2. ሰዎችን ወዲያውኑ አሞግሳቸው ፤
3. ሰዎች ምን ነገር ትክክል እንደሠሩ ንገራቸው ፡ አትንዛዛ ፤
4. ሰዎች ትክክል በሠሩት ነገር ምን ያህል እንደ ተደሰትክና ይኸውም ድርጅቱንና እዚያ የሚሠሩትን ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚጠቅም ንገራቸው ፤
5. የመርካትህን ስሜት ለማስገንዘብ ለአንድ አፍታ ጸጥ ብለህ ቁም ፤
6. በተመሳሳይ መንገድ ጥረታቸውን እንዲገፉበት አበረታታቸው ፤
7. በድርጅት ውስጥ ስኬታማ ውጤት እንዲያገኙ የምትደግፍ መሆንህን ለመግለጽ ያህል ሰዎችን ዳበስ አድርጋቸው ፤ወይም እጃቸውን ጨብጥ ።

«ሦስተኛው ምሥጢር ምንድን ነው?» ሲል ወጣቱ በመጓጓት ጠየቀ ።



ሌቪ በወጣቱ ጉጉት ሣቅ ብሎ ፡ ከመቀመጫው ብድግ አለና ፡ «ወይዘሮ ብራውንን ለምን አትጠይቃቸውም? እርሳቸውን ለማነጋገር ዕቅድ እንዳለህ ዐውቃለሁ» አለ ።

«አዎን ፡ አለኝ» በማለት አረጋገጠለት ወጣቱ ። «እሺ ...... ጊዜህን ለእኔ በመሠዋትህ ከልብ አመሰግንሃለሁ ።»

«ምንም አይደለም» አለው ሌቪ ፡« ተትረፍርፈውኛል ከምላቸው ነገሮች አንዱ ጊዜ ነው ። እንደ ምታየው ፡ እኔ ራሴ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ሆኛለሁ ።»

እንግዳውም ፈገግ አለ ። ይህን አባባል ቀደም ሲልም ከሌላ ቦታ ሰምቶት ነበር ።

ስለ ቀሰማቸው ትምህርቶች ማሰላሰል ፈለገ ። ከሕንፃው ወጣና በአቅራቢያው በሚገኘው አንድ የሕዝብ መናፈሻ ውስጥ ይንሸራሸር ጀመር ። በሰማው ነገር ቀላልነትና ግልጽነት እንደገና ተደነቀ ። «ሰዎች አንድን ነገር በትክክል ለመሥራታቸው ማመስገን ውጤትን ማሳደጊ አያከራክርም» ሲል አሰበ ወጣቱ ፡ በተለይ ምን እንደሚሠሩና ጥሩ የሥራ አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ካወቀ በኋላ ።

«ነገር ግን ፡ ያንድ ደቂቃ ሙገሳ በእርግጥ ተግባራዊ ይሆናልን» በማለት ተጠራጠረ ። «ያንድ ደቂቃ ሥራ አመራር የሚባለውስ ተጨባጭ ውጤት በእርግጥ ያስገኛል ?»

በመንሸራሸር ላይ እንዳለ ይህን ጉዳይ የማወቅ ጉጉቱ እየጨመረ ሔደ ። ስለዚህ ወደ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ጸሐፊ ፣ ወደ ወይዘሮ ሜትካልፍ ቢሮ ተመልሶ በሚቀጥለው ቀን ጥዋት ከወይዘሮ ብራውን ጋር ቀጠሮ እንድትይዝለት ጠየቃት ።

«ነገ ጥዋት ይመቻቸዋል» አለችው ጸሐፊዋ ስልኩን እንዳስቀመጠች ። እንዲያውም ከረቡዕ ጥዋት በስተቀር በፈለከው ጊዜ መምጣት እንደምትችል ንገሪው ብለውኛል ወይዘሮ ብራውን ።»

ሌላ ቅርንጫፍ ድርጅት ቀጠሮ እንዲያዝለት ስለ ጠየቃት ወደዚያው ስልክ ደወለችለት ። ለማነጋገር የፈለገው በዚያ መሥሪያ ቤት የሚገኙትን ባለሥልጣን ፣ ወይዘሮ ጆንስን ነበር ። «በእኛ ሥር ስለሚተዳደሩትና በልዩ ልዩ ቦታዎች ስለሚገኙት ማምረቻዎቻችን ሁሉ መረጃዎች አሏቸው» አለች ወይዘሮ ሜትካልፍ በልበሙሉነት ። «የምትሻውን ማንኛውንም ጉዳይ ከእርሳቸው ማግኘት እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ ። »እርሱም አመሰግኗት ወጣ ።



## ግ ም ገ ማ

ከምሳ በኋላ ወጣቱ በቀጠሮው መሠረት ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ ሔደ ። እዚያም ከወይዘሮ ጆንስ ጋር ተገናኘ ። ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውና የ40 ዓመት ገደማ ሴት ይመስላሉ ። ወደ መጣበት ጉዳይ በመግባት ወጣቱ ፣ «በአገሪትዋ ውስጥ ካሉት ማምረቻዎቻችሁ ሁሉ ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማው የቱ እንደሆነ ሊነግሩኝ ይችላሉ?» ሲል ጠየቀ ። «ክንዋኔዎቻችሁ ቀደም ሲል ካነጋገርኳቸው ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ከተሰኙት ሰው አመራር ጋር መጣጣሙን ለማወቅ እፈልጋለሁ ።»

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ ወይዘሮ ጆንስ የሚከተለውን ሲናገሩ በመስማቱ ሣቀ ። «ደህና ፣ ለማወቅ እምብዛም ውጣ ውረድ አይገጥምህም ። ምክንያቱም ይህም ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ድርጅት ነው ። ልዩ ሰው ናቸው ፣ አይደሉም? በሥራቸው ከሚተዳደሩት ድርጅቶች ሁሉ እርሳቸው ያሉበት የበለጠ ቀልጣፋና ውጤታማ ነው ።»

«ለማመን ያዳግታል» አለ ወጣቱ ፣ «እርሳቸው ከሌሎች ሁሉ የላቀ ጥበብ አላቸው ማለት ነው?»

«የላቸውም» አሉ ወይዘሮ ጆንስ ።

«ደህና ፣ አንድ ዘዴ መኖር አለበት » አለ ወጣቱ ፣ አሁንም በሽማግሌው የአመራር ስልት ግራ በመጋባት ። «እስቲ ይንገሩኝ ፣ ለመሆኑ ብዙ ሰዎች ጥለዋቸው ይሔዳሉ? መሥሪያ ቤቱንስ የሚለቁት ሰዎች መጠን ምን ያህል ነው?»

«አዎ አዎ» አሉት ወይዘሮ ጆንስ ፣ » ብዙ ሠራተኞች መሥሪያ ቤቱን ለቅቀው ይሔዳሉ ።»

«አሃ!» አለ ወጣቱ ፣ አዲስ ነገር ያገኘ መስሎት።

«ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ዘንድ ለቅቀው የሚሔዱት ሰዎች ምን ይሆናሉ?» ሲል ወጣቱ ለማወቅ ፈለገ ።

«የየራሳቸውን ሥራ ያከናውናሉ» በማለት ወይዘሮ ጆንስ በፍጥነት መለሱለት።«ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለሁለት ዓመታት ካላቋረጡ የሥራ አስኪያጅነት ሥራ ይፈልጉላቸዋል ። ለሠራተኞቻችን ሁሉ ከማንም የበለጡ አሠልጣኞችን እርሳቸው ናቸው ። አንድ ክፍት ቦታ ተፈጥሮ ጥሩ ሥራ አስኪያጅ ሲያስፈልግ ይደወልላቸዋል ። ምን ጊዜም ዝግጁ የሆነ ሰው አላቸው ።»

እየተገረመ ጊዜያቸውን ስለ ሠውለት ወይዘሮ ጆንስን አመሰገነ ። ነገር ግን በዚህ አጋጣሚ ከወትሮው የተለየ መልስ አገኘ ።

«ዛሬ ቀጠሮ ሰጥቼህ ላነጋግርህ በመቻሌ ደስ ብሎኛል» አሉት ። «ሳምንቱን በሙሉ በእውነት



ሥራ ይበዛብኛል ። ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁን የአመራር ምሥጢሮች ጠንቅቂ ባውቅ ምንኛ ደስ ባለኝ ። ቢሮዋቸው ድረስ ሔጄ ላነጋግራቸው እየፈለግሁ ፣ ጨርሶ ጊዜ አጣሁ ።»

ወጣቱም ፈገግ እያለ ፣ «እነዚያን ምሥጢሮች እኔ ራሴ ከደረስኩባቸው በኋላ እንደ ስጦታ አበረክትልዎታለሁ ፤ እርሳቸው እንዳበረከቱልኝ ሁሉ» አላቸው ።

«ይህንን ብታደርግማ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ስጦታ እንዳበረከትክልኝ እቆጥረዋለሁ» አሉት ወይዘሮ ጆንስ ፈገግ ብለው ። የተጨናነቀ ቢሮዋቸውን ተመለካከተውም ፣ «የማገኘውን ማንኛውንም ርዳታ ጥቅም ላይ አውለዋለሁ ።»

ወጣቱ ከወይዘሮ ጆንስ ቢሮ ወጣና ራሱን እየነቀነቀ ወደ መንገዱ ገባ ። ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅነት ዘዴ ሙሉ በሙሉ ማርኮታል ።

በዚያን ሌሊት ወጣቱ እንቅልፍ በዐይኑ ሳይዞር አደረ ። ስለሚቀጥለው ቀን እያሰላሰለ በደስታ ሲቃ ተዋጠ ፤ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ሦስተኛውን ምሥጢር የሚቀስምበት ዕለት ነበርና ።

## ሦስተኛው ምሥጢር

### የአንድ ደቂቃ ግሣጼ

በሚቀጥለው ጠዋት ልክ በ3 ሰዓት ወይዘሮ ብራውን ቢሮ ደረሰ ።

ዕድሚያቸው ወደ 50 ዓመት መጨረሻ የሆነና አለባበሳቸው የደመቀ ሴት በሰላምታ ተቀበሉት ። «የተለዩ ሰው ናቸው ፣ አይመስሉህም?» የሚለው የተለመደ ጥያቄ ተደገመለት ። ሆኖም ባሁኑ ጊዜ ወጣቱ ከልቡ ፣ «አዎን ፣ ናቸው» የሚልበት ደረጃ ደርሷል ።

«ስላንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅነት ነግረውሃል?» ሲሉ ጠየቁት ወይዘሮ ብራውን ።

«እስካሁን በየቦታው የምሰማው ይህንኑ ነው» አለ ወጣቱ እየሣቀ ። ምናልባት የተለየ መልስ ይገኝ እንደሆነ በማለት ፣ «የሚታመን አይደለም ፣ ነው እንዴ?» ብሎ ጠየቀ ወጣቱ ።

«ማመኑ ይበጅሃል ። ከእርሳቸው ጋር የተገናኘንበት ጊዜ እንኳ እምብዛም ነው ።»

«ከየሳምንት ስብሰባችሁ ውጭ ከሳቸው ጋር ምንም ያህል ግንኙነት የለኝም ነው የሚሉኝ?» በማለት ወጣቱ ጥያቄውን ቀጠለ ።



«በጣም አነስተኛ ነው ። ለዚያውምኮ ስሕተት ሠርቼ ስገኝ ነው» ሲሉ መለሱለት ወይዘሮ ብራውን ።

ወጣቱ በአነጋገራቸው ተሸማቅቆ ፣ «ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ጋር ግንኙነት የሚኖራችሁ ስሕተት በሠሩ ጊዜ ብቻ ነው?» የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው ።

«አዎ ፣ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ። ግን ነው ለማለት ይቻላል» ሲሉ ወይዘሮ ብራውን መለሱለት ።

«እኔ ደግሞ የመሥሪያ ቤታችሁ ቁልፍ መመሪያ አንድ ሰው ትክክለኛ ነገር ሲሠራ ማግኘት ነው የሚል መስሎኝ ነበር» አለ ወጣቱ ።

«ትክክል ነው» አሉ ወይዘሮ ብራውን ፣ «ነገር ግን ስለ እኔ አንዳንድ ነገር ማወቅ ይኖርብሃል ።»

«ምን ይሆን?»

«እዚህ የሠራሁት ለጥቂት ዓመታት ነው ። ተግባሬን ከላይ እስከ ታች በዝርዝር ዐውቃለሁ ። በመሆኑም ፣ ጊዜ ቢኖራቸው እንኳ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ለግብ ቅየሳ ሲሉ ጊዜያቸውን ከእኔ ጋር ማሳለፍ የለባቸውም ። እንዲያውም ፣ ብዙውን ጊዜ የራሴን የሥራ ግቦች እኔው አርቅቄ እልክላችኋለሁ ።»

«እያንዳንዱ ግብ በተለያዩ ገጾች ላይ ነው የሚመዘገበው?» በማለት ወጣቱ ጠየቀ ።

«እንዴታ ከ250 ባልበለጡ ቃላት ስለሚሰፍር እያንዳንዱን ለማንበብ እኔ ሆንኩ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ከአንድ ደቂቃ በላይ አይፈጅብንም ።»

«ሌላው ስለራሴ መግለጽ የምወደው ቁም ነገር ሥራዬን በጣም እወደዋለሁ ። ስለሆነም ፤ የሚገባኝን ያንድ ደቂቃ ሙገሳ እኔው ለራሴ በራሴ እፈጽማለሁ ። ‘ለራስሽ ካላሰብሽ ፣ ማን ያስብልሻል!’ እያልኩ ለራሴው ማውጠንጠኔን ወድጀዋለሁ ። አንድ ጓደኛዬ የነገረኝ ቁም ነገር ሁልጊዜ ትዝ ይለኛል ፤ ይኸውም ‘የራስሽን ጥሩምባ አንቺው ካልነፋሽው ሌላው ያክታ ማጠራቀሚያ ያደርገዋል’ የሚል ነው ።

ወጣቱም ፈገግ አለ ። ቧልታቸው አስደሰተው ። «ለመሆኑ ፣ ሥራ አስኪያጅዎ አመስግንዎት ያውቃሉ?» ሲል ጠየቃቸው ።

«አንዳንድ ጊዜ ያመሰግኑኛል ፤ ግን አዘውትረው ይህንን ማድረግ የለባቸውም ። ምክንያቱም እቀድማቸዋለሁ» በማለት ወይዘሮ ብራውን መለሱለት ። «አንድ የተለየ ጥሩ ነገር ካከናወንኩ ፤ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ እንዲያሞግሱኝ እኔው እጠይቃቸው ይሆናል ።»

«ይህን ለማድረግ ከቶውኑ እንዴት ድፍረት ይኖርዎታል?» አለ ወጣቱ ። «ቀላል ነው ። ልክ ውርርድ ገብቼ እንደምረታ ወይም ዋናዬን እንደማገኝ ያህል ነው የምቆጥረው ። የሚያሞግሱኝ ከሆነ ፣ ረታሁ ማለት ነው ።»



«ማን ካላሞገስዎትስ?» በማለት አቋረጣቸው ወጣቱ ።

«እንዲያም ከሆነ ዋናዬን ይገፍ ቀረሁ» ሲሉ መለሱለት ወይዘሮ ብራውን ።

ወጣቱም ፈገግ እያለ የወይዘሮ ብራውንን ፍል ስፍና በማስታወሻው ላይ ከመዘገበ በኋላ ጥያቄውን ቀጠለ ።

«ከእኔ ጋር የተወሰነ ጊዜ የሚያሳልፉት አንድ ስሕተት የሠራሁ እንደሆን ነው ብለዋል ። ምን ማለትዎ ነው?» አላቸው ።

«የጐላ ጥፋት ከሠራሁ ፣ ያለጥርጥር የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ይሰነዘርብኛል» ሲሉ ወይዘሮ ብራውን መለሱለት ።

«ምን አሉኝ?» አለ ወጣቱ ደንገጥ ብሎ ።

«የአንድ ደቂቃ ግሣጼ» በማለት ወይዘሮ ብራውን ደገሙለት ። «የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ሦስተኛው ምሥጢር ይኸው ነው ።»

«እንዴት ነው በተግባር የሚተረጐመው?» ሲል ወጣቱ ድምፁን ከፍ አድርጐ ጠየቃቸው ።

«ቀላል ነው» አሉ ወይዘሮ ብራውን ።

«እንዲህ እንደሚሉኝ ገምቻለሁ» አለ ወጣቱ ።

ወይዘሮ ብራውን ስለምን እንደሚናገሩ ወጣቱ ያውቃል ። በተቻለው ፍጥነት ማስታወሻ ይወስድ ነበር ። እኚህ ሴት ብዙ ቁም ነገሮችን ለመግለጽ ረጅም ጊዜ እንደማይፈጅባቸው ተሰማው ።

«በመጀመሪያ» አሉ ወይዘሮ ብራውን ፣ «አብዛኛውን ጊዜ ግዛዎቻቸው የሚሰነዘርብኝ አንድ ስሕተት እንደ ሠራሁ ወዲያውኑ ነው ። ሁለተኛ፣ ጥፋቴን በግልጽ ለይተው መንገራቸው ሥራዬን በዝርዝር በማወቃቸው ነውና ከተዝረከረኩ ከርሳቸው እንደማላመልጥ ዐውቃለሁ ። ሦስተኛ ፣ የሚቆጡኝ በጥፋቴ በመሆኑ ለመከላከል ሙከራ አላደርግም ። ጥፋቴን በእርሳቸው ወይም በሌላ ሰው በማላከክም ማምለጫ ምክንያት ለመፍጠር አልፈልግም ። ሁሉንም ባንድ ዐይን የሚመለከቱ ትክክለኛ ሰው መሆናቸውን ዐውቃለሁ ። አራተኛ ፣ አያወላውሉም ።»

«ይህ ማለት በሌላ ቦታ ቢሳካላቸውም፣እርስዎ ካጠፉ በጥፋትዎ ከመገሠፅ ወደኋላ አይሉም ማለት ነው?» ሲል ጠየቀ ወጣቱ ።

«አዎን» በማለት መለሱለት ወይዘሮ ብራውን ።

«ይህ ሁሉ በአንድ ደቂቃ ውስጥ የሚከናወን ነው?» አለ ወጣቱ ።

«አብዛኛውን ጊዜ.....» አሉ ወይዘሮ ብራውን ። «ካለፈ አለፈ ነው ። የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ረጅም ጊዜ አይፈጅም ፤ ግን እመነኝ አትረሳውም ። ያንን ዐይነት ስሕተትም ደግመህ ከመሥራት ትቆጠባለህ ።»



«ምን ማለትዎ እንደሆነ ይገባኛል» አለ ወጣቱ ። «አንድ ቀን የጠየቅኋቸው ይመስለኛል .....»

«የነገሩህን እንዲደግሙልህ እንዳልጠየቅህ ተስፋ አደርጋለሁ» አሉ ወይዘሮዋ ጣል.ቃ በመግባት ።

ወጣቱም ዐፈረ ። «ጠይቄያለሁ» በማለትም አመነ ።

«እንግዲያው የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ተቀባይ ሰው ምን እንደሚሰማው ታውቃለህ!» አሉ ወይዘሮዋ። «ምናልባት እንግዳ ስለ ነበርክ የተሰነዘረብህ ግሣጼ መለስተኛ ይሆን ይሆናል ።»

«መለስተኛ ይባል እንደሆነ እንኳን አላውቅም» አለ ወጣቱ ። ግን የተናገሩትን ነገር እንዲደግሙልኝ ዳግመኛ የምጠይቅ አይመስለኝም ። እንዲያ ማድረጌ ስሕተት ነበር ። ለመሆኑ» አለ እንግዳው ፣ «የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ስሕተት ይሠሩ ይሆን? ፍጹም የሆኑ ሰው ይመስላሉ ።»

ወይዘሮ ብራውን መሣቅ ጀመሩ ። «ይሳሳታሉ ለማለት እንኳን አልደፍርም» አሉ ወይዘሮዋ ። «ነገር ግን ቀልደኛ ናቸው ። እናም የግሣጼውን የመጨረሻ ግማሽ የመርሳት ዐይነት ስሕተት ቢሠሩ ፣ እኛው እስታውሰናቸው እንቀልድባቸዋለን ። ይህንን የምናደርገውም ከግሣጼያቸው ለማንሰራራት ጊዜ ካገኘን በኋላ ነው ። ለምሳሌ ቆየት ብለን ስልክ እና ደርግላቸውና መሳሳታቸውን እንደ ተገነዘብን እንነግራቸዋለን ። ከዚያም ምናልባትም ሣቅ እያልን የግሣ

ጊያቸውን የመጨረሻ ግማሽ ፣ ማለት ሙገሳቸውን ባለመስማታችን ቅሬታችንን በመግለጽ ያን እንዲያ ጊሉልን እንጠይቃቸዋለን ።»

«እናስ ምን ያደርጋሉ?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ።

«አብዛኛውን ጊዜ ይሥቁና መልካም ሰው ስለ መሆኑ ሳያወሱልኝ በመዘንጋታቸው ይቅርታ ይጠይቃሉ ።»

«በሙገሳውም ፣ በግሣጼውም መሣቅ ትችላለችኋ?» አለ ወጣቱ ።

«እንዴታ!» አሉ ወይዘሮ ብራውን ። «እየሀ ፣ ስሕተት በሠራን ጊዜ በራሳችን መልሰን መሣቅ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ አስተምረውናል ። ይህም ሥራችንን በንጹሕ ልቡና እንድንቀጥል ይረዳናል ።»

«ግሩም ነው» ሲል ወጣቱ የአድናቆት ስሜቱን ገለጸ ። «ለመሆኑ ይህን እንዴት ለመማር ቻላችሁ?»

«በቀላሉ» በማለት መለሱ ወይዘሮ ብራውን ። «አለቃችን ራሳቸው በራሳቸው ላይ ሲፈጽሙት በማየትና ፈለጋቸውን በመከተል ነው ።»

«አለቃችሁ ቢሳሳቱ በራሳቸው ላይ መልሰው መሣቅ ይችላሉ ነው የሚሉኝ?» ሲል የተደነቀው ወጣት ጠየቃቸው ።

«አይ ፣ ሁልጊዜ እንኳን አይደለም» አሉ ወይዘሮ ብራውን ። «እርሳቸውም ቢሆኑ እንደ አብዛኛዎቻችን ናቸው ። አንዳንድ ጊዜ ይከብዳቸዋል ። ዐልፎ ዐልፎም ቢሆን ከማድረግ አይቆጠቡምና በራሳቸው መሣቃቸውን የተመለከተ በአቅራቢያቸው የሚገኝ ማንም ሰው ትምህርታዊ መልእክት ያገኝበታል ።»



«በራሳቸው በጣም የሚተማመኑ ሰው መሆን አለባቸው» አለ ወጣቱ ።

«ናቸው» በማለት አረጋገጡለት ወይዘሮ ብራውን ።

ወጣቱ ስለ ሰውዬው ከፍተኛ ግምት አደረበት ። እንደዚህ ያለ ሥራ አስኪያጅ ለአንድ ድርጅት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይታየው ጀመር ።

«ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ግሣጼ ይህን ያህል ውጤታማ የሆነው ለምን ይመስሎታል?» ወጣቱ ጠየቀ ።

«ይህንን ጥያቄ ለአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ብታቀርብ እወዳለሁ» በማለት ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ወጣቱን ለማሰናበት ወደ በሩ መሩት ።

ጥያቄዎቹን በመመለስ ላባከኑት የሥራ ጊዜያቸው ወጣቱ ቢያመሰግናቸው ፣ ወይዘሮ ብራውን ፈገግ ብለው ፣ «ለዚህ መልሱ ምን እንደሚሆን መገመት ትችላለህ» አሉት ። ሁለቱም ሣቁ ። እንደ ጕብኚ ሳይሆን የመሥሪያ ቤቱ 'አባል' እንደሆነ ይሰማው ጀመረ ። የሚያስደስት ነው ።

ከቢሮው ወጣ ብሎ መንገድ እንደ ጀመረ ፣ ከሴትየዋ ጋር ያሳለፈው ጊዜ አጭር ቢሆንም ያገኘው መረጃ ከፍተኛ መሆኑን አስተዋለ ።

ሴትየዋ ስለነገሩት ነገር አሰላሰለ ። በጣም ቀላል ይመስላል ። አንድ ታታሪ ሰው ስሕተት ሠርቶ ቢገኝ ምን መደረግ እንዳለበት በአእምሮው አብላላ ።

## ያንድ ደቂቃ ግሣጼ ማጠቃለያ

የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ጥሩ ውጤት የሚያስገኘው የሚከተሉት ሲሟሉ ነው ።

1. ሰዎች ሥራቸውን እንዴት ባለ ሁኔታ ማከናወን ላይ እንዳሉ በማያሻማ ቋንቋ በቅድሚያ ግለጽላቸው ።

<u>የግሣጼው የመጀመሪያ ግማሽ</u>

2. ሰዎችን ወዲያውኑ ገሥፅ ።
3. ምን ስሕተት እንደሠሩ ንገራቸው — አታንዛዛ።
4. ስለ ሠሩት ስሕተት ምን እንደ ተሰማህ ግልጽ በሆኑ ቃላት ንገራቸው ።
5. ለጥቂት ደቂቃዎችም ጸጥ በማለት ስሜትህ ጠልቆ እንዲሰማቸው ጊዜ ስጣቸው ።

<u>የግሣጼው ሁለተኛ ግማሽ</u>

6. ከልብ የምትደግፋቸው መሆንህን በሚያሳይ መንገድ እጃቸውን ጨብጥ ወይም ዳሰስ አድርጋቸው ።
7. ስለ እነርሱ ምን ያህል ከፍተኛ ግምት እንዳለህ አስገንዝባቸው ።



8. በስሕተታቸው ቅር ብትሰኝም ፣ ስለ እነርሱ በጐ አመለካከት እንዳለህ እንደገና አረጋግጥላቸው።
9. ግሣጼው አንዴ ከተሰጠ በኋላ ያከተመለት መሆኑን ልብ በል ።

ወጣቱ ራሱ በተጨባጭ ስለ አንድ ደቂቃ ግሣጼ ውጤት ልምድ ባያገኝ ኖሮ ፣ ውጤታማነቱን አምኖ ለመቀበል ያዳግተው ነበር ። ጭንቀት ተሰምቶት እንደነበር አያጠራጥርም ። እናም ያ ሁኔታ እንደገና እንዲገጥመው አልፈለገም ።

ይሁን እንጂ ፣ ማንም ሰው ዐልፎ ዐልፎ ስሕተት መሥራቱ እንደማይቀር ያውቃልና እርሱም አንድ ቀን ከግሣጼ እንደማያመልጥ ተገንዘበ ። ግን ግሣጼው የሚሰነዘርበት ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ከሆነ ተገቢ እንደሚሆን አምኗል ። ምክንያቱም ሰብዕናውን ሳይሆን አድራጐቱን የሚመለከት ስለሚሆን ነው ።

ወደ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ሲገሠግሥ ፣ የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ፅንሰ ሐሳብ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ያሰላስል ነበር ።

ሦስቱም ምሥጢሮች — ማለት የአንድ ደቂቃ ግብ ፣ የአንድ ደቂቃ ሙገሳና የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ሁሉም ከልብ የሚደርሱ ናቸው ። «ግን የሚፈለገውን ውጤት ለምን ያስገኛሉ!» ሲል ተገረመ ።

«በኩባንያው ውስጥ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ከሁሉ የበለጠ ለምን ምርታማ ሆነ?»

## የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ያስረዳል

የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ እንደ ደረሰ ጸሐፊዋ ፣ «በቀጥታ መግባት ትችላለህ ። እንዲያውም መቼ ተመልሰህ እንደምታነጋግራቸው ጓጉተዋል» አለችው ።

ወጣቱ ገባ እንዳለ ፣ ቢሮው ከዚህ ቀደም እንዳየው ሁሉ ጽዱና ያልተዝረከረከ መሆኑን አስተዋለ ። የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁም በደመቀ ፈገግታ ተቀበሉት ።

«ደህና ፣ ካደረግከው ጉብኝት ምን አገኘህ?» ሲሉ ጠየቁት ።

«ብዙ ነገር» በማለት ወጣቱ በጋለ መንፈስ መለሰላቸው ።

«ተማርኩ የምትለውን ነገር ንገረኝ» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ በማደፋፈር ጠየቁት ።

«ራስዎን በራስዎ ለምን የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ብለው እንደሚጠሩ ለማወቅ ችያለሁ ። ሠራተኞችዎ ተጠያቂ የሚሆኑበት የሥራ ውጤት ምን እንደሆነና ጥሩ የሥራ አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ማወቃቸውን ለማረጋገጥ የአንድ ደቂቃ ግቦች ከባልደረባዎችዎ ጋር ትቀይሳላችሁ ። ከዚያም የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ለማበርከት አንድ ነገር ትክክል



መከናወኑን ለማየት ይሞክራሉ ። እናም ከመጨረሻ ፣ አንድ ነገር በትክክል ለመሥራት አስፈላጊው ችሎታ ሁሉ እያላቸው እን ዲያ ሳያደርጉ ቢቀሩ ያንድ ደቂቃ ግሣጼ ይሰነዝሩባቸዋል ።»

«እነዚህ ሁሉ ምን ይመስሉሃል?» በማለት ያንደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ጠየቁት ።

«ነገሩ ቀላል መሆኑ አስገርሞኛል» አለ ወጣቱ ፣ «ግን በተግባር ላይ ይውላል ፣ ውጤትም ያገኙበታል ። በእርግጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉትም አምኛለሁ ።»

«በተግባር ላውለው ብለህ ብትነሣ ፣ ላንተም ይሠራል» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ያላቸውን አመለካከት ገለጹ ።

«ምናልባት» አለ ወጣቱ ፣ «እኔ በተግባር ላውለው የምነሣሣው ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ ይበልጥ ያወቅሁ እንደሆን ነው ።»

«ማንም ሰው የሚያስበው እንደዚያው ነው ወዳጄ ። ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ በተረዳህ መጠን ፣ የበለጠ ሥራ ላይ ልታውለው ትገፋፋለህ ። ስለዚህ ፣ የማውቀውን ያህል ብነግርህ ደስ ይለኛል ። ከየት እንድጀምርልህ ትፈልጋለህ?»

«ደህና ፣ በመጀመሪያ ፣ የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ሲሉ ፣ በሥራ መሪነትዎ ማከናወን የሚገባዎትን ነገሮች ሁሉ ለመሥራት በእርግጥ አንድ ደቂቃ ብቻ ያስፈልግዎታል ማለትዎ ነው?»

«አይደለም ፣ ሁሌ እንዲያ ሊሆን አይችልም ። የሥራ መሪነት ሰዎች እንደሚያስቡት የተወሳሰበ አለመሆኑን ለማመልከት የተፈጠረ ዘይቤ ነው ። ሰውን መምራት ደግሞ አንተ እንደምታስበው ረጅም ጊዜ አይፈጅም ። ስለዚህ የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ስል ቁልፍ የሆኑት እንደ ግብ ቅየሳ የመሳሰሉትን ተግባሮች ከአንድ ደቂቃ ባላይ ሊፈጁ ይችላሉ ። ግን ቃሉ ቅልጥፍናን ይገልጻል ። አብዛኛውን ጊዜም ክንዋኔው በአንድ ደቂቃ ብቻ ይገባደዳል ።

«በጠረጴዛዬ ላይ ከማስቀምጣቸው ማስታወሻዎች አንዱን ላሳይህ ።» ወጣቱም የሚከተለውን ተመለከተ ።

«ከጊዜዬ ሁሉ ከፍተኛ ግምት የምሰጠው ለሰዎች ዕድገት ያዋልኳትን ደቂቃ ነው ።»

«የተገላቢጦሽ ነው» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «ብዙ ድርጅቶች ከገንዘባቸው ከ50% እስከ 70% ለሰዎች ደመወዝ ያውላሉ ። ግን ሰዎቻቸውን ለማሠልጠን ከበጀታቸው የሚወጣው ከ1% ያነሰ ነው ። እንዲያውም አብዛኞቹ ድርጅቶች ሰዎቻቸውን ከመንከባከብና በሙያቸው እንዲዳብሩ ከማድረግ ይልቅ ይበልጡን ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን የሚያጠፉት ሕንፃዎቻቸውንና መሣሪያዎቻቸውን በመጠጋገን ነው ።»

«ከዚህ በፊት ጨርሶ አላሰብኩበትም ነበር» አለ ወጣቱ ። «ውጤት እስካስገኙ ሰዎች ላይ ማተኮሩ በእርግጥ ተገቢ እርምጃ ነው ።»



«ትክክል» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «ወደ ሥራ ዓለም እንደ ተሠማራሁ አንድ ሰው እንዲያ ቢያደርግልኝ ኖሮ......»

«ምን ማለትዎ ነው?» ጠየቀ ወጣቱ ።

«ደህና ፣ ቀደም ብዬ በሠራሁባቸው በአብዛኞች ድርጅቶች ምን መሥራት እንደሚገባኝ እምብዛም አላውቅም ነበር ። ማንም ሰው ሊነግረኝ አላሰበበትም ። ጥሩ ትሠራ ነበር ወይ ብለህ ብትጠይቀኝ ፣ መልሴ 'አላውቅም' ወይም 'ይመስለኛል' ይሆናል ። ለምን እንደዚህ እንደ ማስብ ብትጠይቀኝ ደግሞ በጥፋት ምክንያት አለቃዬ ቁጣ አላወረደብኝም እንጂ 'እጠብቅ የነበረው ቁጣ ነው' እልሃለሁ ። በዚያን ወቅት ሥራዬን ለማከናወን የምገፋፋው በአመዛኙ ከቅጣት ለማምለጥ ነበር ።»

«እንዲህ ያለውን መስማቱ ደስ ይላል» አለ ወጣቱ ፣ ግን በደንብ የተረዳሁ አይመስለኝም ። እንዲያውም የሚስማሙ ከሆነ ፣ 'ለምን' ወደሚለው ጥያቄዬ ብገባ ነገሮቹን የበለጠ መረዳት እችል ይሆናል ። በአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ እንጀምር ። ይህ ዘዴ ለምን ጥሩ ውጤት ያስገኛል?»

## የአንድ ደቂቃ ቅየሳ ለምን ስኬታማ እንደሚሆን

«የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ውጤት ለምን ስኬታማ እንደሚሆን ለማወቅ ትፈልጋለህ?» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «ጥሩ ነው» ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ወዲያና ወዲህ መንጐራደድ ጀመሩ ።

«ለመረዳት የሚያስችልህ አንድ ምሳሌ ልስጥህ ። ለዓመታት በተቀጠርኩባቸው ልዩ ልዩ ድርጅቶች ውስጥ ብዙ ደንታቢሶች በሥራ ላይ እንዳሉ ለይቻለሁ ። ይሁን እንጂ፤ከሥራ ሰዓት ውጭ አንድም ደንታቢስ ሰው ጨርሶ አጋጥሞኝ አያውቅም ። ማንም ሰው የሆነ ነገር ለማድረግ ግፊት ያለው ይመስላል ።

«ለምሳሌ በመጨረሻ በሠራሁበት ድርጅት ፣ በሥራ ላይ 'አስቸጋሪ ሠራተኞች' ናቸው ከሚባሉት ጥቂቶቹን አንድ ማታ ቦውሊንግ ከምጫወትበት ሥፍራ አገኘኋቸው ። በጣም አስቸጋሪ ከሚባሉት አንዱ ፣ በእርግጥ እኔም በሚገባ አስታውሰዋለሁ ፣ የቦውሊንግ መምቻ ኳስ አነሣና መወርወሪያው ቦታ ድርስ አንከባለለ ። ከዚያም በደስታ እየፈነደቀና እየጮኸ ዙሪያውን መዝለል ጀመረ ። እንደዚህ የተደሰተው ለምን ይመስልሃል?»

«ያሰበውን ውጤት በማግኘቱ ነዋ ! የሚመቱትን ነገሮች በሙሉ መድፋት በመቻሉ ።»



«ትክክል ። ታዲያ እርሱና ሌሎች ሰዎች በሥራ ላይ ለምን እንደዚያ አይነቃቁም?»

«ምክንያቱም ዓላማቸውን ባለማወቃቸው ነው» ሲል መለሰ ወጣቱ ፈገግ ብሎ ። «ይኸው ነው ። ዓላማ ከሌለው ምኑን ተጫወተው?»

«ልክ ነው» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ። «አሁን በአብዛኛዎች ድርጅቶች ምን እንደሚደረግ ማየት ትችላለህ ። ብዙዎች ሥራ አስኪያጆች ሰዎቻቸው ምን ምን ሊያከናውኑላቸው እንደሚፈልጉ ያውቃሉ ብዬ አምናለሁ ። ለሰዎቻቸው ሊገባ በሚችል መንገድ ለማስረዳት አይሞክሩም ። ማወቅ አለባቸው ብለው ይገምታሉ ። ግብ ቅየሳን በተመለከተ እኔ በበኩሌ እነርሱው ይወጡታል ብዬ ጭራሽ አልገምትም ።»

«ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ያውቃሉ ብለህ ከገመትክ ተልካሻ የቦውሊንግ አጨዋወት አመጣህ ማለት ነው ። አንድ ተጨዋች የሚመታቸውን ነገሮች በየቦታቸው ደርድረህለት ተጨዋቹ ኳሱን አንከባልሎ ለመምታት ሲመጣ በወረቀት ተጋርደው ያገኛቸዋል ። ስለዚህ ኳሱን አንከባልሎ በግርዶሹ ሥር ሲያሳልፍ እነዚያን ነገሮች መምታቱ ቢሰማውም ስንቱን እንደ ጣለ አያውቅም ። ምን ውጤት እንዳገኘ ብትጠይቀውም አላውቅም ብሎ ይመልስልሃል ። ግን እርካታ ያገኛል ።

«ጐልፍ በሌሊት የመጫወት ያህል ነው ። ብዙ ወዳጆቼ የጐልፍ ጨዋታ አቋርጠዋልና ለምን

እንዳቋረጡ ስጠይቃቸው ፤ 'በመጫወቻው ቦታ ሰዎች ስለ በዙበት ነው' የሚል ምክንያት ይሰጡኛል ። ማታ ማታ እንዲጫወቱ ሳሳስባቸው ፤ ይሥቃሉ ። ምክንያቱም ወጣ ገባውን አረንጓዴ መስክ ሳይታኝ ማን ጐልፍ ተጫውቶ ያውቃል?

«የእግር ኳስ ጨዋታም እንዲሁ ነው ። ስንት ሰዎች ናቸው በየቴሌቪዥናቸው ፊት ለፊት ተጐልተው ፤ ሁለት ቡድኖች ኳሷን የሚያስገቡበት የግብ ማዕዘኖች በሌሉበት ሜዳ ሽቅብና ቁልቁል ሲራወጡ ብቻ ማየት የሚሹ?»

«አዎ! ለምንድርን ነው?» በማለት ወጣቱ ጠየቀ ።

«ምክንያቱም ፤ የሰዎች ዋነኛው ቀስቃሽ የውጤታቸውን ግምገማ መስማት መሆኑ በግልጽ መታወቅ አለበት ። እንዲያውም ፤ ማስታወስ ያለብን አንድ ዐይነት አባባል አለ ፤ 'ውጤትን ማወቅ ለተሳካላቸው ቁርስ ነው' ይላል ። የሥራችንን ውጤት ማወቅ ያተጋናል ። ይሁን እንጂ ፤ ብዙዎቹ ሥራ አስኪያጆች የሥራ ውጤትን ማወቅ ሰውተግቶ እንዲሠራ ከሚገፋፉት ነገሮች በአንደኛ ደረጃ የሚታይ መሆኑን እያወቁ ፤ አብዛኛውን ጊዜ ሦስተኛ ዐይነት የቦውሊንግ አጨዋወት ደንብ ማዘጋጀታቸው ያሳዝናል ።»

«አንድ የቦውሊንግ ተጨዋች ኳሱን ለማንከባለል ወደ መስመሩ ሲጠጋ የሚመቱት ነገሮች ተደርድረው ፤ ግርዶሽም ተሰቅሎ ያያል ። ግን አሁን



ሌላ ነገር በጨዋታው ውስጥ ታክሎበታል ፤ ይኸውም ከግርዶሹ በስተኋላ ተቆጣጣሪ ሰው ቆሟል ። ተጨዋቹ ኳሱን እንከባልሎ የሚመቱት ነገሮች መውደቃቸውን ቢሰማም ተቈጣጣሪው ሁለት ብቻ መትተህ ጥለሃል ለማለት ሁለት ጣቶቹን ይቀስራል ። በመሠረቱ ፤ አብዛኛዎች ሥራ አስኪያጆች ይህን አግኝተሃል ይላሉ?»

«አይሉም» ሲል ፈገግ አለ ወጣቱ ። «አብዛኛውን ጊዜ የሚቀናቸው ሁሉንም ስተሃል ማለት ነው ።

«ትክክል!» ፤ አሉ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ። «ሁልጊዜ የማነሣው ጥያቄ ቢኖር 'ሥራ አስኪያጁ ግርዶሹን አንሥቶ ፤ ማለትም ራሱና የበታች ሠራተኛው የተከናወኑትን ነገሮች በአንድ ላይ ማየት እንዲችሉ ለምን አያደርግም? ለምን?' የሚል ነው ። 'ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ስለሚዘጋጅለት ነው' ከማለት በስተቀር ሌላ ምክንያት የለኝም ።»

«የሥራ አፈጻጸም ስለሚዘጋጅለት ነው?» አለ ወጣቱ በመደነቅ ።

«አዎን ! እንደዚህ ያሉ ሥራ አስኪያጆች ከሠራተኞቻቸው ምን እንደሚጠብቁ አይነግሯቸውም ፤ እንደዚሁ ስድ ይለቋቸውና ውጤታቸው ከሚጠበቀው በታች ከሆነ ሠራተኞቻቸውን ለማብጠልጠል ያመቻቸዋል ። »

«ለምን እንደዚህ ያደርጋሉ ብለው ይገምታሉ?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ፤ የሥራ አስኪያጁ አባባል ሐቅነት እየከነከነው ።

«ጥሩ መስለው ለመታየት» አሉት ሥራ አስኪያጁ ።

«ጥሩ መስለው ለመታየት ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?» አለ ወጣቱ ።

«ለሠራተኞችህ ሁሉ ከፍተኛ ነጥብ ብትሰጣቸው የቅርብ አለቃህ እንዴት የሚያይህ ይመስልሃል?»

«እንደ ለዘብተኛ ፣ ጠንካራውን ከደካማው መለየት እንደማይችል ።»

«ልክ ብለሃል» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «በአብዛኞች ድርጅቶች ውስጥ ጥሩ ሥራ አስኪያጅ መስለህ ለመታየት ፣ ከሠራተኞህ አንዳንዶቹን ስሕተት ሲሠሩ እጅ ተፍንጅ መያዝ አለብህ ። ጥቂት የተሳካላቸውንና እንዲሁም ጥቂት ያልተሳካላቸውን ደርድረህ የቀሩትን በሁለቱ መኻከል አስፍራቸው ። እየህ ፣ 'የተለመደ — ስብጥር—ኩርባ' (ኖርማል—ዲስትሪቢዩሽን—ከርቭ) እምነት ተዋሕዶናል» አሉት ። አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ ፣ ልጄ የሚማርበትን ትምህርት ቤት ስጐበኝ ፣ አንዲት አስተማሪ የጂኦግራፊ ፈተና ስትሰጥ ደረስኩ ። ለምን እትላስ አስቀምጣላቸው ልጆቹ ያንን እየተመለከቱ ፈተናውን እንደማይሠሩ ብጠይቃት ፣ 'ይህንን ማድረግ አልችልም፤ ምክንያቱም ልጆቹ ሁሉ 100 በ100 ያገኛሉ' የሚል መልስ ሰጠችኝ ። ሁሉም ደህና ውጤት ማምጣታቸውን እንደ መጥፎ ነገር ተመልክታዋለች ።

«እንዴ ያነበብኩት ትዝ ይለኛል ። አንስታይንን አንድ ሰው የቤቱን ስልክ ቁጥር ቢጠይቀው ፣ አንስ



ታይን ቁጥሩን ለማግኘት ስልክ ማውጫ አነሣ ይባላል ።»

ወጣቱም ማቀና ፣ «ቀልድዎን ነው?» አለው ።

«የቀልዴን አይደለም ። በቀላሉ ለሚያገኘው መረጃ ጭንቅላቱን አጣብቦ እንደማያውቅ ለሰው ዬው ነገረው ይባላል ።»

«አሁንም አንተ እንዲያ ያለውን ግለሰብ ማንነቱን ሳታውቅና» ቀጠሉ ሥራ አስኪያጁ ፣ «የራሱን ስልክ ቁጥር ባለማስታወሱ በማውጫ ሲፈልግ ብታገኘው ምን ትለዋለህ? ትክክለኛ ወይስ የተምታታበት ሰው ብለህ ታስባለህ?»

ወጣቱም በፈገግታ፣ «በእርግጥም የተምታታበት ነው እለዋለሁ» ሲል መለሰ ።

«አዎ ትለዋለህ» አሉ ሥራ አስኪያጁ ፤ «እኔም ብሆን እንዲሁ እለዋለሁ ። ግን ተሳስተናልኮ ፣ አልተሳሳትንም?»

ወጣቱም ራሱን ከፍና ዝቅ በማድረግ መስማማቱን ገለጸላቸው ።

«ማንኛችንም እንዲህ ያለው ስሕተት ውስጥ በቀላሉ እንገባለን» አሉት ሥራ አስኪያጁ ። ከዚያ በኋላ ለራሳቸው ያዘጋጁትን መርሕ አሳዩት ። «ይህንን እስቲ ተመልከት ።

«ማንም ሰው የስኬታማነት እምቅ ኃይል አለው ። አንዳንዶች ግን የማይሳካላቸው ይመስላሉ ፤ ግን በገጽታቸው አትታለል ።»

«አየህ» አሉ ሥራ አስኪያጁ ፣ «በሥራ አስኪያጅነትህ ሦስት አማራጮች ይኖሩሃል ። አንደኛው ፣ ቀደም ሲባል ስኬታማ ውጤቶች ያስመዘገቡትን መቅጠር ትችላለህ ። እነዚህን ማግኘትና መቅጠር ከባድ ከመሆኑም በላይ ብዙ ወጭ ያስወጣሃል ። ወይም ሁለተኛው ፣ እንዲያ ያሉትን ማግኘት ካልቻልክ ፣ የስኬታማነት እምቅ ኃይል ያላቸውን መቅጠር ነው ። ከዚያም እነዚህን ሰዎች በሥርዓት አሠልጥነህ ውጤታቸው እንዲሠምር ማድረግ ነው ። ከእነዚህ ከሁለቱ አማራጮች በአንዱም ለመጠቀም ካልፈቀድክ ፣ የሚቀርህ ሦስተኛው ምርጫ ጸሎት ይሆናል ።

የሥራ አስኪያጁ አነጋገር ወጣቱን አስደነገጠው ። ማስታወሻውንና ብዕሩን አስቀምጦ «ጸሎት?» ሲል ጠየቃቸው ።

ሥራ አስኪያጁም ሣቅ ብለው «እንዲሁ ላሥቅህ ብዬ ነው ይህንን ያልኩት ፣ ወዳጄ ። ባይገርምህ በየቀኑ የሚጸልዩ ብዙ ሥራ አስኪያጆች አሉ — 'የቀጠርኩት ሰው የሚሳካለት እንዲሆን እርዳኝ' እያሉ ።»

«እዬ!» አለ ወጣቱ ኮስተር ብሎ ። «ይልቅስ ፣ እስቲ የመጀመሪያውን ምርጫ እንመልከት ። ቀደም ሲባል ስኬታማ ውጤት ያሳዩትን ሰዎች መቅጠር ፣ እርግጥም በቀላሉ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ያስችላል ፣ አይመስልዎትም?»



ሥራ አስኪያጁም ፈገግ ብለው «ትክክል ነው» አሉት ። ወጣቱ ነገሩን አሁን ምን ያህል አጥብቆ መከታተል እንደያዘ ተገረሙ ። «አስቀድሞ የተሳካላቸውን ሰዎች ብታገኝ የአንድ ደቂቃ ግብ በጋራ ትቀይሳላችሁ ። ከዚያም ሥራቸውን ራሳቸው እንዲከታተሉ ማድረግ ትችላለህ ።»

«ከወይዘሮ ብራውን የተረዳሁት እንዳንዴ ግቡን አብራችሁ እንደማትቀይሱ ነው» አለ ወጣቱ ።

«የነገረችህ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው» አሉት ሥራ አስኪያጁ ። «እዚህ አካባቢ ካሉት አብዛኞቹ ሰዎች ችሎታዋ ሳይታወቅላት የተረሳች ነች ። ግን ለማንም ሰው ፣ አስቀድሞ የተሳካለት ይሁን ወይም ወደፊት ሊሳካለት የሚችል ፣ የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ለውጤታማ የሥራ ክንውን ዐይነተኛ መሣሪያው ነው ።»

«የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ ማንም ያዘጋጀው ፣ እያንዳንዱ ግብ ሁልጊዜ በአንድ ገጽ ወረቀት ላይ መስፈር አለበት?» ሲል ጠየቀው ወጣቱ ።

«ያላንዳች ጥርጥር» በማለት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ አረጋገጡለት ።

«ይህን ያህል ለምን አስፈላጊ ሆነ?»

«ሰዎች ግባቸውን አዘውትረው እንዲመለከቱና የሥራ አፈጻጸማቸውን ከቀየሱት ግብ ጋር ለማመሳከር እንዲችሉ ለመርዳት ነዋ !»

«እርስዎ አበክረው የሚጠይቁት የበታች ሠራተኞችዎ ዋና ዋና የሥራ ግቦቻቸውንና ኃላፊነታቸ

ውን ብቻ እንጂ ፣ ጥቃቅን ሥራዎቻቸውን ሁሉ መጻፍ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ» አለ ወጣቱ ።

«አዎን ! ምክንያቱም የወረቀት ክምር እንዲሆን ፍላጎት የለኝም ። ብዙ ወረቀቶች አንድ ቦታ እንዲከማቹና በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለሚቀጥለው ዓመት ግብ ቅየሳ ፣ ወይም ለሥራ አፈጻጸም ግምገማ ፣ ወይም ለሌላ ለሆነ ጉዳይ ሲባል እንዲታዩ አልፈልግም ።»

«ምናልባት አይተህ ይሆናል ፣ የሥራ ባልደረቦቹ ሁሉ ካጠገባቸው ይህን የመሰለ መርሕ አስቀምጠዋል» አሉት የራሳቸውን እያሳዩት ።

«ለአንድ ደቂቃ ያህል ፤
ግቦችህን ተመልከት ፤
የሥራ አፈጻጸምህን አስተውል ፤
ከንዋኔህ ከግብህ ጋር መጣጣሙን አገናዝብ።»

ወጣቱ ተገረመ ። በዚች በአጭር ጉብኝቱ ይህን አላየም ነበር ። «ጭራሽ ልብ አላልኩትም» አለ ወጣቱ ። «ድንቅ ነው ። አንዱን ቢሰጡኝ?»

«እንዴታ !» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «እንዲመመጣልህ አደርጋለሁ ።»

ከቀሰመው ትምህርት አንዳንዱን በማስታወሻው ላይ እያሰፈረ እጩው ሥራ አስኪያጅ አንገቱን ቀና ሳያደርግ ፣ «እንደሚያውቁት በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ ስለ አንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ጠንቅቆ መማር አዳጋች ነው ። ለምሳሌ ፣ ስለ አንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ በሰፊው ለማወቅ እፈልጋለሁ ፤ ግን ይህንን እንኳን ኋላ እመለስበት ይሆናል ። አሁን ወደ አንድ



ደቂቃ ሙገሳ ብንሻገር ምን ይመስልዎታል?» ሲል ጠየቃቸው ወጣቱ አንገቱን ካቀረቀረበት ማስታወሻ ደብተሩ ላይ ቀና አድርጎ ።

«በሚገባ» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ። «ምናልባት የአንድ ደቂቃ ሙገሳም ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ ሳያሳስብህ አልቀረም ።»

«በጣም እንጂ» ሲል መለሰላቸው እንግዳው ።

## የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ

«ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት» አሉ ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ። «ምናልባት ከዚያ በኋላ ያንድ ደቂቃ ሙገሳ ለምን ጥሩ ውጤት እንደሚያስገኝ ግልጽ ይሆንልሃል ።»

«ደስ ይለኛል» አለ ወጣቱ ።

«በመጀመሪያ በአንዲት ርግብ ምሳሌነት ልጀምርና ከዚያ ወደ ሰዎች ልሻገር ። ልብ ቦል ፣ እንዲሁ ለምሳሌ ፣ ያህል ልጠቀምበት እንጂ ሰዎች እንኳ ርግቦች አይደሉም ። ከርግብ ይበልጥ ውስብስብ ናቸው ። ይገነዘባሉ ፤ ለራሳቸው ያስባሉና በሌላ ሰው እንዲወናበዱ አይፈልጉም ።

«ይህንን ቁም ነገር አስተውል ፣ አክብረውም ። ለጥሩ ሥራ አመራር መሠረት ነውና ።

«ይህን ግንዛቤ በአእምሮህ ይዘህ ፣ ሁላችንም ብንሆን የሚስማሙንን ነገሮች ለማግኘት መፈለጋችንና ከማይስማሙን ደግሞ ለመራቅ መሞከራችንን የሚያሳዩ አንዳንድ ቀለል ያሉ ምሳሌዎች እንመልከት ።

«በታችኛው ግራ ማዕዘን በኩል ወደ አንድ ሣጥን ከአስገባሃት በኋላ በሣጥኑ ውስጥ እንዳለች ወደ ላይኛው ቀኝ ማዕዘን ሮጣ አንድ የብረት ዘንግ



በቀኝ እግርዋ እንድትገፋ የምታሠለጥናት አንዲት ርግብ ትኖርሃለች እንበል ። ያ የብረት ዘንግ ከመግቢያዋ እምብዛም ሳይርቅ ጥራጥሬ ከያዘው ከልዩ መሣሪያ ጋር የተገናኘ ሆኖ መሣሪያው ርግቧ ዘንጉን በነካችው ቁጥር ለመካስና ለማትጋት ጥራጥሬ የሚበትን ነው ። እርሷ ግን ይህን አታውቅም ። ስለዚህ ርግቧን ሣጥኑ ውስጥ አስገብተህ ምንም ምግብ ሳትሰጣት ወደ ላይኛው ቀኝ ማዕዘን ሮጣ ዘንጉን በቀኝ እግርዋ እስክትገፋ ብትጠብቅ ምን የምትሆን ይመስልሃል?» በማለት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ጠየቁት ።

«በረኃብ ትሞታለች» አላቸው ወጣቱ ።

«ትክክል ነህ» እንዲህ ከሆነ ብዙ ርግቦች ያልቁብናል ። «ርግቧ በረኃብ የምትሞተውም ምን ማድረግ እንዳለባት ባለመገንዘቧ ነው ።»

«ታዲያ ርግቧ ያን ተግባር እንድታከናውን ማሠልጠን ከባድ አይደለም ። ማድረግ ያለብህ ርግቧ ወደ ሣጥኑ በምትገባበት ፉካ አጠገብ አንድ መስመር ማስመር ነው ። ርግቧ ወደ ሣጥኑ ውስጥ በምትገባበት ጊዜ መስመሩን ስታቋርጥ መኪናው ጥሬውን ይበትንላትና ትመገባለች ። ወዲያውኑ ርግቧ ምግብ ወደምታገኝበት ቦታ ስትሮጥ ታያታለህ ። ግን በዚያው እንድትለምድብህ አትፈልግም ። ታዲያ ርግቧ የት እንድትሆንልህ ትሻለህ?»

«በሣጥኑ ውስጥ በስተቀኝ በኩል በላይኛው ማዕዘን» አለ ወጣቱ ።

«ትክክል!» አሉት ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ። «ስለዚህ ፥ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ርግቧ ወደ ለመደችበት ቦታ ብትሮጥም ምግቧን ታቆምባትና ከአሁኑ መስመር ጥቂት ፈቀቅ ብለህ ሌላ መስመር ታሰምር ላታለህ ። ግን አንተ ወደምትፈልገው አቅጣጫ ቀረብ የሚል መሆን አለበት ፤ ይኸውም ወደ ሣጥኑ ቀኝ ክፍል የላይኛው ማዕዘን ማለት ነው ። አሁን ርግቧ ወደ ቀድሞው ቦታ ትሮጥና ምግቧን ማግኘት ያቅታታል ። ብዙ ሳትቆይ አዲሱን መስመር ስታቋርጥ እንደ ለመደችው መኪናው ምግቡን ይለቅላትና ትመገባለች ።

«እንደገና ሌላ መስመር ታሰምራለህ ። ይህ መስመር አሁንም ወደ ታሰበው ግብ አቅጣጫ ቀረብ ይበል ። ግን ከፊተኛው ርቆ ርግቧ ምግቡን እንዳታገኝ የሚያውክ መሆን የለበትም ። ርግቧ ከላይኛው ቀኝ ማዕዘን ደርሳ የተጋደመውን ዘንግ ካልረገጠች ምግቧን እንዳታገኝ ፥ እነዚህን መስመሮች ጥቂት በጥቂት ከሣጥኑ በስተቀኝ በኩል ወደሚገኘው የላይኛው ማዕዘን እያስጠጋን ፥ እንዲያውም በመጨረሻ በቀኝ እግሯ ስትረግጠው ብቻ ምግቧን ማግኘት እንድትችል እናደርጋለን ።»

«እነዚህ ትንንሽ ግቦች ለምን ይቀየሳሉ?» ወጣቱ ለመረዳት ጠየቀ ።

«መስመሮቹን ትንሽ በትንሽ ስናንፏቅቅ ፥ ርግቧ ማግኘት የሚኖርባትን ግቦች እየቀየስንላት ነው ። አንድ ሰው አዲስ ነገር እንዲሠራ የማሠልጠን መሠረቱ በመጀመሪያ ፥ የታቀደለትን ተግባር



የመሰለ ሥራ እንዲያከናውን መርዳት ፤ ከተወሰነ ልምምድ በኋላም ሙሉ በሙሉ እንደሚፈለገው አስተካክሎ እንዲሠራው ማድረግ ነው ።»

«ይህንን ፅንሰ ሐሳብ ልጆችን ስናስተምርና እንስሳትን ስናሠለጥን ሁልጊዜ በተግባር እናውለዋለን ። ግን ዐዋቂዎችን ስናስተምር ችላ እንለዋለን ። ለምሳሌ ፥ የባሕር እንስሳት ትርዒት እንዲያሳዩ በሚደረጉባቸው ኩሬዎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ትርዒቱ የሚያልቀው አንድ በጣም ትልቅ ዓሣ ነባሪ ከውሃው በላይ የተዘረጋውን ገመድ እንዲዘል በማድረግ ነው ። ዓሣ ነባሪው ገመዱን ዘሎ ውሃው ላይ ተመልሶ ሲያርፍ እስከ 10 መደዳ የተቀመጡ ሰዎችን ያጥለቀልቃል ።

«ሰዎቹ ከዚያ ትርዒት ሲመለሱ ፥ «ይህ የሚታመን ነገር አይደለም ። ያንን ዓሣ ነባሪ እንዴት ቢያሠለጥኑት ነው እንዲህ የሚዘረው?» እያሉ በየግላቸው ያጉተመትማሉ ።

«አሠልጣኞቹ በጀልባ ወደ ውቅያኖስ ሔደው ፥ ለዓሣ ነባሪው በውሃው ላይ ገመድ ዘርግተው ፥ ‘ዝለል! ዝለል’ በማለት ከውሃ ውስጥ ወጣ ብሎ ገመዱን እስኪዘል የሚጮሁ ይመስልሃል?» አሉት ሥራ አስኪያጁ ። ከዘለለላቸው በኋላም ‘እንዲያ ነው! እንምረጠው ፥ የሚፈለገው እሱ ነው ።’

«አይመስለኝም ። ይኸማ የሠለጠነን መቅጠር ይሆናል» በማለት ወጣቱ እየሣቀ መለሰላቸው ።

ሁለቱም ተንከተከቱ ።

«በመጨረሻም ሕፃኑ ፣ በሚደረግለት እንክብካቤ ይደሰትና ደግሞ ደጋግሞ እየተውተረተረ መራመዱን ቀጥሎ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በእግሩ ቆሞ መሔድ ይችላል ።

«ሕፃን እንዲናገር ለማስተማር በተመሳሳይ ዘዴ እንጠቀማለን ። ለምሳሌ አንድ ሕፃን ፣ 'አንድ ብርጭቆ ውሃ ስጠኝ' እንዲል ለማስተማር ትፈልጋለህ እንበል ። ሕፃኑ ዐረፍተ ነገሩን አስተካክሎ መናገር እስኪችል ድረስ ከጠበቅህ ፣ ሕፃኑ በመካከል በውሃ ጥም ይሞታል ። ስለዚህ ቃሉን ለማለማመድ ፣ 'ውሃ ፣ ውሃ በል' ትለዋለህ ። ከዕለታት አንድ ቀን በድንገት ፣ 'ዋ' ሲል ትሰማለህ ። በዚህን ጊዜ ከደስታ ብዛት ከመቀመጫህ ብድግ ትላለህ ። ሕፃኑን አቅፈህ ትስመውና ለአያቱ ስልክ ደውለህ ፣ 'ልጄ ዋ ማለት ቻለ' ብለህ ትነግር ይሆናል ። ይህ 'ውሃ' ማለት አይደለም ። ቢሆንም ለዚያ በጣም ቀረብ ይላል ።

«አሁን ሐያ አንድ ዓመት የሞላው ጐልማሳ አንድ ምግብ ቤት ገብቶ አንድ ብርጭቆ 'ዋ' ቢል አትቀበለውም ፣ ከተወሰነ ዕድሜ በኋላ 'ውሃ' ማለት ይገባዋልና ። 'እባክዎ' የሚል የክበሬታ ቃል እንዲጨምርበትም ታደርገዋለህ ።

«እነዚህ ምሳሌዎች የሚያስረዱን ዋናው ቁም ነገር ፣ ማንኛውንም ሰው ሥራው እንዲሳካለት ልና ሠለጥን በትክክል መሥራቱን እንድናረጋግጥ ነው ። በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ ባይዋጣለትም ቀስ በቀስ ከሚጠበቅበት ደረጃ እንዲደርስ እናደርጋለን ። ንቁ



የሆነን ሰው መሥራት አለመሥራቱን አዘውትሮ ለማረጋገጥ መሞከር ይህንን ያህል አስፈላጊ ሳይሆን ይችላል ። ምክንያቱም እንደዚህ ያለ ሰው በትክክል መሥራቱን ስለሚገነዘብ ለበለጠ ውጤት ራሱን ማሠልጠን ይችላል ።»

«በዚህ ምክንያት ነው አዲስ ሠራተኞች ገና ሥራ ሲጀምሩ ወይም ልምድ ያካበቱ ነባር ሠራተኞች አዲስ ፕሮጀክት ሲሰጣቸው እርስዎ በቅርብ አጥብቀው የሚቆጣጠሩዋቸው?» በማለት ወጣቱ ጠየቀ ።

«አዎን» አሉ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ። «ብዙ ሥራ አስኪያጆች ሠራተኞቻቸው በሚጠበቀው የጥራት ደረጃ መሥራት እስኪችሉ ከማሞገስ ይቆጠባሉ ። በዚህ የተነሣ ፣ ብዙ ሠራተኞች ከተፈለገው ደረጃ ጨርሶ መድረስ ሳይችሉ ይቀራሉ ። ምክንያቱም አለቆቻቸው የሚያተኩሩት ስሕተት ሲሠሩ ለማግኘት — ማለትም ከሚጠበቅባቸው ግብ ሳይደርሱ የቀሩ እንደሆነ ለመተቸት ስለሚቋምጡ ነው ። ወደ ርግቧ ምሳሌ መለስ ብንል እንዲህ ያለው አቀራረብ ርግቧን ሣጥን ውስጥ አስገብቶ ዘንጉን በራሷ ጥረት ረግጣ ምግቧን እስክታገኝ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ያን እንድትፈጽም ለመገፋፋት የሚነዝራት ኮረንቲ በሣጥኑ ዙሪያ አጥምዶ እንደ መቅጣት ይቆጠራል ።»

«የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ አይሆንም» ሲል ወጣቱ ግንዛቤውን ገለጸ ።

«እንደምትለው ነው» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ። «ርግቧ ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቷን

ብትቀበልም ምን መሥራት እንደሚጠበቅባት (የብረቱን ዘንግ መርገጥ እንዳለባት) ስለማታውቅ ፣ በሳጥኗ ውስጥ በአንደኛው ጥግ ትኮራመታለች ። ያለችበት አካባቢ አጥፊዋ መስሎ ስለሚታያት ጉዳት ላይ ላለመውደቅ እንቅስቃሴ ከማድረግ ትቈጠባለች ።»

«ይህ ድርጊት ልምድ በሌላቸው አዲስ ተቀጣሪዎች ላይ ዘወትር የምንፈጽመው ነው ። በደስታ እንቀበላቸዋለን ፣ ከቢሮ ቢሮ እያዟዟርን እናስተዋውቃቸዋለን ፣ ከዚያ በኋላ ለብቻቸው እንተዋቸዋለን ። ተግባራቸውን ከሞላ ጐደል በትክክል ማከናወናቸውን እንኳ አለመገንዘባችን አንሶ ዐልፎ ዐልፎም እንዲተጉ በነገር እንጐተጉታቸዋለን ። ይህ የተለመደ የአመራር ስልት ነው ። ይህን ስልት 'አግለህ — ዝለፈው' እንለዋለን ። ሠራተኛህን ለብቻው ትተህ ጥሩ ውጤት እንዲያበረክት ትጠብቅበትና ያሰብከው ሳይሆን ሲቀር ትዘልፈዋለህ ።»

«የእንዲህ ያለው ሰው መጨረሻው ምን ይሆን?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ።

«ማንኛውንም ድርጅት ብታይ ፣ እንደምረዳው ብዙዎቹን ጐብኝተሃል» ፣ አሉት ሥራ አስኪያጁ ፣ «ምን እንደሚሆኑ ታውቃለህ ፣ ምክንያቱም አይተሃቸዋል ። በአመዛኙ እንዲያ ያሉት ሰዎች ዳተኞች ይሆናሉ ።»

ዛሬ የብዙዎች ድርጅቶች ችግርም ይኸው ነው ። በብዛትም በጥራትም ሰዎቻቸው የችሎታቸውን ያህል አያመርቱም ። ለዚህም ድክመት ዋናው ምክንያት አምራቾቹ የሚያገኙት ደካማ አመራር ነው ።»



ወጣቱ የማስታወሻ ደብተሩን አስቀመጠ ። አሁን ስለ ሰማው ነገር አሰበ ። የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ምንነት — ተጨባጭ የምርት መሣሪያነቱ ይታየው ጀመር ።

እንደ አንድ ደቂቃ ሙገሳ የመሰለ ቀላል ነገር በሥራ ዓለም ውስጥም ሆነ ውጭ ውጤት ማስገኘቱ አስገረመው ።

«ትምህርትዎ የሆኑ ጓደኞቼን አስታወሰኝ» አለ ወጣቱ ። «ስልክ ደውለው አንድ ውሻ ለማሳደግ ያላቸውን ዕቅድ ነገሩኝ ። ውሻውን እንዴት እንደሚያሠለጥኑት ስለአላቸው ዘዴም ምን እንደማስብ ጠየቁኝ ።»

ሥራ አስኪያጁም ለመጠየቅ እየፈሩ ፣ «እንዴት እናሠለጥናለን አሉህ?» አሉት ።

«ውሻው በድንገት ምንጣፍ ላይ ቢያመልጠው ፣ እየጐተቱት በጣለው ቆሻሻ ውስጥ አፍንጫውን ከነከሩ በኋላ በጋዜጣ መታ አድርገውት መጸዳዳት ወዳለበት ወደ አትክልት ቦታ በመስኮት ይወረውሩታል ።

«ከዚያም ፣ ይህ የአሠለጣጠን ዘዴ ስለሚኖረው ውጤት አስተያየቴን ጠየቁኝ ። ምን እንደሚሆን ስለማውቅ ከት ብዬ ሣቅሁ ። ከሦስት ቀናት ያህል በኋላ ውሻው በተከለከለው ቦታ ይጸዳዳና በመስኮት

ዘሎ ይወጣል ። ውሻው ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም ። ግን ከዚያ አካባቢ መጥፋት እንዳለበት ተገንዝቧል ።»

ሥራ አስኪያጁም አድናቆታቸውን አስተጋቡለት ። «የሚገርም ታሪክ ነው» አሉት ። «አየህ ፤ በራሱ በማይተማመን ወይም ልምድ ስለሌለው ሰው ላይ የሚፈጸም ቅጣት ውጤቱ ይኸው ነው ። የሥራ ልምድ የሌላቸው ሰዎች የምንፈልገውን የሥራ ውጤት ማስገኘት ካልቻሉ ፤ ከመቅጣት ይልቅ ወደ አንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳ መለስ ብለን የሚጠበቅባቸው ውጤት ምን እንደሆነ መረዳታቸውን እናረጋግጣለን። እነርሱም ጥሩ የሥራ አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ይገነዘባሉ ።»

«ደህና ፤ ታዲያ የአንድ ደቂቃ ግብ ከተቀየሰላቸው በኋላ፤አሁንም ያን የተባለውን ነገር ከሞላ ጎደልም ቢሆን በትክክል መሥራታቸውን ለማወቅ ትሞክራላችሁ» ሲል ወጣቱ ጠየቃቸው ።

«በሚገባ!» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ጥያቄውን መለሱለት ። «ምንጊዜም ቢሆን ገና ከመጀመሪያው የአንድ ደቂቃ ሙገሳ ልትሰጥ የምትችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ታደርጋለህ ።» ቀጥሎም ወጣቱን ትኩር ብለው ዐይን ዐይኑን እየተመለከቱ ፤ «የነገሩህን በፍጥነት የምትረዳና የበለጠ ለማወቅ የምትጓጓ ተማሪ ነህ ። የአንድ ደቂቃ የሥራ አመራር ምሥጢሮችን ከአንተ ጋር መካፈሉ ደስ ይለኛል » አሉት ። ሁለቱም ፈገግ አሉ ። የአንድ ደቂቃ ሙገሳን ምንነት በሚገባ ተገንዝበላቸዋል ።



«እኔም ምን ጊዜም ቢሆን ከግሣጼ ይልቅ ሙገሳን እመርጣለሁ» አለ ወጣቱ እየሣቀ ። «አሁን የአንድ ደቂቃ ግብ ቅየሳና የአንድ ደቂቃ ሙገሳ የሚፈለገውን ውጤት ለምን እንደሚያስገኙ የተረዳሁ ይመስለኛል ። በዕውነት የሁለቱም ጠቃሚነት ተሰምቶኛል ።»

«ጥሩ ነው» አሉ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ።

«ግን የአንድ ደቂቃ ግሣጼ እንዴት ውጤት እንደሚያስገኝ ገና ለመረዳት አልቻልኩም» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ወጣቱ ጠየቀ ።

«ስለ እሱ እስቲ ጥቂት ላውሳልህ» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ።

## የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ለምን ውጤት እንደሚያስገኝ

«የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ጥሩ ውጤት የሚያስገኝ ባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው ።

«በመጀመሪያ» አሉ ሥራ አስኪያጁ ሲያስረዱት፣ «የአንድ ደቂቃ ግሣፄ መልዕክት ፈጣን ነው ። 'ጥፋቱ' ን እንዳየህ ወይም መረጃ እንዳገኘህ ግለሰቡ ዘንድ ወዲያው ትደርሳለህ ። ቂም ማካበት አግባብ አይደለም ።

«ለአንድ ደቂቃ ግሣፄ ስኬታማነት የምላሹን ፍጥነት መገንዘብ ትልቅ ትምህርት ነው ። ጥፋት እንደ ተሠራ በተቻለ መጠን ወዲያው የዲስፕሊን እርምጃ ካልተወሰደ ፣ ለወደፊት ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይሠራ ለማረም እምብዛም አይረዳም ። ብዙዎች ሥራ አስኪያጆች የሚያዩትን ድክመት ያከማቹና አንድ ቀን በሥራ አፈጻጸም ግምገማ ላይ ወይም በተበሳጩ ዕለት የመዘገቡትን የጥፋት ዝርዝር እንድም ሳይቀራቸው ይዘከዝካሉ ። ባለፈው ሳምንት ወይም ወር ወይም ከዚያ በፊት የተሠራውን ጥፋት ሁሉ አንድ ባንድ ይዘረዝራሉ ።»

ወጣቱ በረጅሙ ተነፈሰና ፣ «ሐቅ ነው» አላቸው ።



«ከዚያም» በማለት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ገለጻቸውን ቀጠሉ ፤ «አለቃና ጭፍራ ሙግት ይገጥማሉ ፣ ወይም ይቀያየሙና በዝምታ ይፋጠጣሉ። ግሣፄ የሚደርስበት ሠራተኛ ምን ስሕተት እንደሠራ በፍጹም አያውቅም ። ይህ ቀደም ብዬ የነገርኩህ የ'አግለህ — ዝለፈው' ዲስፕሊን ሥርዓት እንዱ ገጽታ ነው ።»

«የሚሉኝ ይገባኛል» ሲል መለሰ ወጣቱ ፤ «በእውነት ልርቀው የምፈልገው ተግባር ነው ።»

«እንዴታ» አሉት ሥራ አስኪያጁ ። «ሥራ አስኪያጆች አንድ ጥፋት እንደ ተሠራ ወዲያው እርምጃ ቢወስዱ ፣ በአንድ ወቅት አንድ ስሕተት በማስወገዳቸው ተግሣፅ የሚደርስበት ሰው በጭንቀት አይዋጥም ። ምላሽም ያገኛሉ ። ስለዚህ ነው የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚቀርብ ግባር ሳይሆን ፣ ያለማቋረጥ የሚቀጥል ክንዋኔ መሆን ያለበት ሒደት ነው የምለው ።»

«የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ውጤት የሚያስገኝበት አንደኛው ምክንያት ግሣፄውን የሚቀበል ሰው የሠራውን ጉድለት መገንዘብ ይችላል ፤ ምክንያቱም ሥራ አስኪያጁ የሚያነሣበት፣በአንዲት ወቅት አንድ ጥፋት ብቻ ነው ። ተገቢና ግልጽ ይሆናል» ሲል ወጣቱ ንግግሩን አጠቃለለ ።

«አዎን» አሉ ሥራ አስኪያጁ ። «በሁለተኛ ደረጃ ፣ የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ሲሰጥ የሰውን ሰብእና በምንም መንገድ አልነካም ። ግሣፄውን የሚቀበሉ

ሰብእናቸው ስለማይነካባቸው መከላከል አለብን አይሉም ። የተሠራው ስሕተት ላይ ብቻ ነው የማተኩረው ። በመሆኑም የግሣጼዬ አቅጣጫም ሆነ የሰዎቹ ግላዊ አቋም በድርጊቱ ላይ የሚያነጣጥር እንጂ የየራሳቸውን ስሜቶች ለየስብእናቸው ሲሉ የሚያብጠለጥሉበት መድረክ አይሆንም ።

«ሥራ አስኪያጆች በሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወስዱ ብዙውን ጊዜ ግለሰቡን ይወነጅላሉ ። የኔ ዓላማ በአንድ ደቂቃ ግሣጼ ጥፋቱን ማስወገድና ግለሰቡን መንከባከብ ነው ።»

«በዚህ ምክንያት ነዋ የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ሁለተኛ ክፍል ወደ ሙገሳ የሚለወጠው» አለ ወጣቱ ። «ውጤታቸው ባይሰምርም ምስጋና ያገኛሉ ማለት ነው ።»

«እርግጥ ነው» በማለት ያንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ መስማማታቸውን ገለጹለት ።

«ለምን ሙገሳውን አስቀድመው ግሣጼውን አያስከትሉም ?» አላቸው ወጣቱ

«በሆነ ምክንያት ፣ ያ አይሠራም» ሲሉ መለሱለት ሥራ አስኪያጁ ባለማወላወል ።«አንዳንድ ሰዎች ፣ ለእኔም አሁን ነው የገባኝ ፣ በሥራ አስኪያጅነቴ ቅንና ኃይለኛ ሰው ነው ይሉኛል ። በእርግጥም እኔ እንደዚያ ያለሁ ሰው ነኝ ። »

«ኃይለኛና ቅን ሰው?» በማለት ወጣቱ የሥራ አስኪያጁን ቃላት አስተጋባ ።



«አዎን» አሉት ሥራ አስኪያጁ አቋማቸውን አጠናከረው ።» ይህ ለብዙ ሺ ዓመታት ሥራ ላይ ውሎ ውጤት ሲያስገኝ የኖረ የአመራር ፍልስፍና ነው ።»

«እንዲያውም በጥንታዊት ቻይና ይህንን የሚያመለክት አንድ አፈ ታሪክ አለ ። በአንድ ዘመን ይኖር የነበረ አንድ ንጉሥ ረዳት የሚሆነው ሰው ሾመ ። ይህንን ጠቅላይ ሚኒስትሩን አስጠራውና ‘ሥራዎቻችንን ለምን አንከፋፈልም? አንተ ቅጣት ስትሰጥ እኔ ደግሞ ሽልማት ባበረክትስ?’ አለው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ፣ ‘ጥሩ! እኔ እቀጣለሁ ፤ እርስዎ ይሸልሙ’ የሚል መልስ ሰጠው ።»

«ይህን ታሪክ ልወደው ነው» አለ ወጣቱ ።

«ትወደዋለህ ፣ ትወደዋለህ» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ በፈገግታ ። «አሁን ይህ ንጉሥ» በማለትም ንግግራቸውን ቀጠሉለት።«ንጉሡ አንድ ነገር ባዘዛቸው ቁጥር ከፊሉ ትእዛዙን ሲፈጽሙ ፣ የቀሩት ደግሞ እንደማይፈጽሙ አስተዋለ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲናገር ግን ሁሉም ሽር ጉድ ይላሉ ። ንጉሡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንደገና አስጠራውና ‘ሥራችንን እንደገና ለምን አንከፋፈልም? ለተወሰነ ጊዜ አንተ ስትቀጣ ቆይተሃል። አሁን ደግሞ እኔ ስቀጣ አንተ ሸልም’ አለው ። በዚህ አኳኋን ንጉሡና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ድርሻቸውን ተለዋወጡ ።

«በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተወዳጅ ሆነ ። ንጉሡ የሚሾምና የሚሸልም ፣ ግሩ

ምና ለሁሉም ደግ እንዳልነበረ ሁሉ ፣ በድንገት የቅጣት በትሩን በሰዎች ላይ መዘዘ ። ሕዝቡም ‘ይህ ነጭናጫ ሽማግሌ ምን ነካው?’ አለ ። ጊዜ አልፈጀበትም ፤ ከዙፋኑ ላይ አሽንቀጥሮ ጣለው ። በቦታውም ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንነሡበት ።»

«እውነተኛ ታሪክ ነው?» ሲል ወጣቱ ጠየቀው ።

«እውነት ሆነ አልሆነ ምን አስጨነቀህ?» በማለት የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ እየሣቁ መለሱለት ። «ወደ ቁም ነገሩ እንመለስና ፣ መልእክቱ ግልጽ ነው ። በመጀመሪያ ጥብቅ ብትሆንና በኋላ ግን ላላ በማለት ሠራተኛህን ብትደግፍ ያዋጣሃል ።»

«ባለንበት ዘመን ፣ ከሥራ አመራር ውጭ የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ውጤት ያስገኘበት ቦታ እንዳለ ምሳሌ ሊሰጡኝ ይችላሉ?» ሲል ወጣቱ ሥራ አስኪያጁን ጠየቃቸው ።

«አዎን ፣ በሚገባ እንጂ » አሉት ። «እንዲያውም ሁለት ምሳሌዎች ልስጥህ — አንዱ በከፍተኛ ደረጃ የተበላሸ ጐልማሳን ሰው ጠባይ ለማረም ሲረዳ ሌላው ልጆችን ሥነ ሥርዓት እንዲጠብቁ ማድረግ ነው ።»

«‘በከፍተኛ ደረጃ የተበላሸ የዐዋቂ ሰው ጠባይ’ ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?» አላቸው ወጣቱ ።

«በተለይም የመጠጥ ሱሰኞችን ማለቴ ነው» በማለት ሥራ አስኪያጁ መለሱለት ። የዛሬ ሠላሳ ዓመት ገደማ አንድ አስተዋይ ቄስ ባሁኑ ጊዜ በተግባር የሚፈተንና ‘ችግር እንደ መፍትሔ’ የሚባል



አንድ ስልት አገኙ ። ያገኙትም ሆስፒታል የተኛች የአንድ ሐኪም ሚስት በመርዳት ላይ እንዳሉ ነበር ። ሴትየዋ ሆስፒታል የገባችው ከሞት አፋፍ ባደረሳት በጉበት በሽታ ነበር ። ሆኖም የመጠጥ ሱሰኛነቷን አምና አልተቀበለችም ። ቤተሰቦቿ በአልጋዋ ዙሪያ እንደ ተሰበሰቡ በመጠጥ ኃይል ተሸንፋ ያዩባትን ሁኔታዎች አንድ በአንድ እንዲገልጹላቸው ቄሱ ጠየቁ ። ይህ ለአንድ ደቂቃ ግሣፄ ዋነኛ መሠረት ነው ። ግሣፄ ከመሰንዘርህ በፊት የተሠራውን ጥፋት በግልጽ ማየት አለብህ — ሌላ ሰው በሚለው መተማመን የለብህም ። የምትሰጠውን ተግሣፅ በአሉባልታ ላይ አትመሥርት ።»

«ይገርማል» በማለት ወጣቱ ጣልቃ ገባ ።

«የጀመርኩትን ልጨርስልህ ። ቤተሰቦቿ አድራጐቶቿን ካብራሩላቸው በኋላ እያንዳንዳቸው ስለ አድራጐቶቿ የተሰማቸውን ለራሷ እንዲነግሯት ቄሱ ጠየቋቸው ። ከበብዋት ። በመጀመሪያ ምን ምን እንዳደረገች ፣ ቀጥሎም በዚያን ጊዜ የተሰማቸውን ስሜት ተራ በተራ ገለጹላት ። ተቆጥተዋል ፣ ተባሳተዋል ፣ አፍረዋል ። ከዚያ በኋላ ምን ያህል እንደሚወድዋት እየነገርዋትና በስሜት እየደባበስዋት የዕድሜ ባለጸጋ ሁና እንደገና አስደሳች ሕይወት እንደ ሚኖራት ያላቸውን ምኞት ገለጹላት ። የሚቆጧትም በዚሁ ምክንያት እንደነበር አሳወቋት ።»

«በጣም ቀላል ይመስላል» አለ ወጣቱ ። «በተለይም የመጠጥ ሱስን ለሚያህል ውስብስብ ችግር ። ታዲያ ሙከራቸው ሠራ?»

«በሚያስደንቅ አኳኋን!» ሲሉ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ አረጋገጡለት ። «በእርግጥ ሙከራው እንዲህ ቀላል አልነበረም ። ግን እነዚህ ሦስቱ መሠረታዊ ነገሮች ፣ ማለትም ለሰዎች ምን ጥፋት እንደሠሩ መንገር ፣ ስለጥፋቱ ምን እንደ ተሰማህ መግለጽና አጥፊዎች ጠቃሚና አስፈላጊ መሆናቸውን ማስረዳት — የሰዎችን ጠባይ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።»

«ከልብ የሚደርስ ሐሳብ ነው» አለ ወጣቱ ።

«እንዴታ» በማለት ሥራ አስኪያጁ ተስማሙ ።

«ቀደም ሲሉ የአንድ ደቂቃ ግሣጼን ስልቶች ሌሎች ሰዎች እንዴት ለስኬታማነት እንደሚያውሏቸው ሁለት ምሳሌዎች እሰጥሀለሁ ብለውኝ ነበር» አለ ወጣቱ የልጆችን ጠባይ ለማረቅ እንዴት እንደሚጠቀም ለመረዳት ፈልጎ ።

«አዎ ፣ በርግጥ ብዬሃለሁ በ1970 መጀመሪያ በካሊፎርኒያ ውስጥ አንድ የአዕምሮ ሐኪም (ሳኪያትሪስት) በልጆችም ላይ ይህንኑ ድንቅ ግኝት አረጋግጧል ። ስለ ሕብረት — ስለ ሰዎች ጥልቅ የእርስ በርስ መተሳሰብ — ብዙ አንብቧል ። ሰዎች ምን እንደ ሚፈልጉ ያውቃል ። ሰዎች ከሰዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ፣ በሌሎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ይፈልጋሉ ።

«ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ስለ አንድ ነገር ምንነት እቅጩን ለማወቅ ይጣጣራሉ ። በተለይም ያስቡልናል የሚሏቸው ሰዎች ከስሕተት እንዲያድኗቸው እንደሚሹ ሐኪሙ ተገንዝቧል ።».



«ይህን እንዴት በተግባር ማረጋገጥ ይቻላል?» ሲል ወጣቱ ጠየቀ ።

«ልጅ ሲያጠፋ እያንዳንዱ ወላጅ ልጁን በማስጠጋት ፣ ማለት እጁን በትከሻው ላይ በማድረግ ፣ ክንዱን በመንካት ፣ እንዲያውም ሕፃን ከሆነ ጭን ላይ በማስቀመጥ የወላጅነትን ስሜት ማሳየት ተገቢ ነው ። ከዚያም ወላጅ በማያሻማ ቋንቋ ልጁ የሠራውን ጥፋትና ወላጅም በወላጅነቱ የተሰማውን ስሜት መግለጽ ይኖርበታል ። (እንደምታየው የታመመችው ሴት ቤተሰብ አባላት ካደረጉት ጋር በጣም ይመስላል ።) በመጨረሻም ወላጅ በረጅሙ ይተነፍስና ለጥቂት ሴኮንዶች በዝምታ ይዋጣል ልጁ እንዲሰማው ለማድረግ ። ከዚያ በኋላ ወላጅ ልጁ ለወላጆቹ ምን ያህል ብርቅዬና ተፈላጊ እንደሆነ ማብራራት አለበት ። የየራሱን ጠባይ የሚቆጣጠር ሰው ማፍራት ነው ቁምነገሩ ።

«እንግዲህ ይህንን ያህል ካወቅህ» አሉት ሥራ አስኪያጁ ከሚወዷቸው መርሖች ወደ አንዱ እያመለከቱት ፣ «የስኬታማ ግሣጼን መሠረተ ሐሳብ ጨበጥክ ማለት ነው ።

«እኛ የጠባያችን ነጸብራቅ ብቻ አይደለንም ጠባያችንን የምንመራም ሰዎች እንጂ ።

«ጥፋታቸውን ፣ በቅርበት የምትከታተል ብቻ ሳትሆን ሰዎችን የምትመራም መሆንህን ከተገነዘብክ ፣ አመራርህ ይሠምራል» በማለት ሥራ አስኪያጁ ንግግራቸውን አጠቃለሉ ።

«በእንደዚህ ያለ ግሣጼ ውስጥ ሰዎችን የመንከባከብና የማክበር አዝማሚያ ያለ ይመስላል» አለ ወጣቱ ።

«ይህንን በማስተዋልህ በጣም ደስ ብሎኛል ። የምትገሥፀውን ሰው ደኅንነት ከልብህ ካሰብክበት ያንድ ደቂቃ ግሣጼ ስኬታማ ይሆንልሃል ።»

«ይህ አንድ ነገር ያስታውሰኛል» አለ ወጣቱ ። «ኢቶ ሌቪ እንደ ነገረኝ በሙገሳ ወቅት ድጋፍዎን ለማሳየት ትክሻ መታ መታ ያደርጋሉ ፤ ወይም እጅ ይጨብጣሉ ፤ ወይም በሌላ በሆነ መንገድ ከሰውነት ጋር ንክኪ ይፈጥራሉ ። አሁንም ወላጆች በሚቆጡበት ወቅት የልጆቻቸውን አካል እንዲዳስሱ ሲያበረታቱ ይታየኛል ። ንክኪ የአንድ ደቂቃ ሙገሳና ግሣጼ ዋና ክፍል መሆኑ ነው?»

«መልሴ አዎን እና አይደለም ነው» በማለት ሥራ አስኪያጁ በፈገግታ መለሱ ። «አዎን የምለው ፤ ሰውዬውን ደኅና አድርገህ የምታውቀው ከሆነና ለወደፊትም ሥራው እንዲሳካለት በእርግጥ ለመርዳት ፍላጎት ሲኖርህ ነው ። አይደለም የምለው ደግሞ ፤ አንተ ወይም ሰውዬው ጥርጣሬ ሲኖራችሁ ነው ።»

«ንክኪ በጣም ኃይለኛ መልዕክት አለው» ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ጠቆሙት ። «የትኛውም ንክኪ ከፍተኛ ስሜት ያመነጫልና ድርጊቱ ጥንቃቄን ያሻል ። ለምሳሌ አቋሙ የሚያጠራጥርህ ሰው በሙገሳ ወይም በግሣጼ ወቅት እንዲነካህ ትፈቅድለታለህ?»



«አይ» ሲል ወጣቱ በግልጽ መለሰላቸው ። «በፍጹም አላደርገውም!»

«ምን ማለቴ እንደሆን ገባህ?» አሉት ሥራ አስኪያጁ በጥሞና ። «ንክኪ በጣም ሐቀኛ መግለጫ ነው ። ሰዎች ስትነካቸው እነርሱን ለመንከባከብ ብለህ ወይም በአዲስ ዘዴ ልታሽከረክራቸው ሙከራ የምታደርግ መሆኑ ወዲያው ይገባቸዋል ።

«ስለንክኪ አንድ ቀላል ሕግ አለ» በማለት ገለጻቸውን ቀጠሉ ሥራ አስኪያጁ ። «የምትነካቸው እምነት ፣ ድጋፍ ፣ ማበረታቻ .....ለበጐ ጐኖቻቸው ስታበርክትላቸው ብቻ መሆ ን ይኖርበታል ።

«ስለዚህ አንድ ሥራ አስኪያጅ ሰዎቹን እስኪያውቃቸውና እነርሱም እርሱ ስለስኬታማነታቸው ማሰቡን — ማለትም ከጐናቸው መቆሙን እስኪገነዘቡለት ድረስ ከንክኪ መቆጠብ አለበት ማለት ነው?» ሲል ወጣቱ ጠየቃቸው ።

«አዎ ፣ ነው እንጂ ።»

«ግን» በማለት እያመነታ ቀጠለ ፣ «የአንድ ደቂቃ ሙገሳና የአንድ ደቂቃ ግሣጼ ሲመለከቷቸው ቀላል ዘዴዎች ይመስላሉ ። ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ድርጊቶች እንዲያከናውኑ የሚገፋፉ ኃይለኛ መሣሪያዎች መሆናቸው አይካድም ። በአጉል መሸንገል እንዳይተረጐሙ ጥንቃቄው ምንድን ነው?»

«የአንድ ደቂቃ ሙገሳና ግሣጼ ሰዎች የሚጠበቁባቸውን ድርጊቶች እንዲያከናውኑ የሚያደርጉ ኃይለኛ መሣሪያዎች ናቸው ያልከው እርግጥ ነው» በማለት ሥራ አስኪያጁ ሐሳቡን ደገፉለት ።

«ይሁን እንጂ ፡ መሸንገል ሰዎች የማያውቁትን ወይም የማይስማሙበትን ነገር ማሠራት ነው ። በዚህ ምክንያት ነው እያንዳንዱ ሰው ከመጀመሪያው ምን እንደሚያደርግና ለምን እንደማያደርግ በግልጽ ማሳወቁ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ።»

«እንደ ማንኛውም የሕይወት ገጠመኝ ነው» አሉት ሥራ አስኪያጁ ። «በተግባር ላይ ሲያውሏቸው ውጤት የሚያስገኙ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ፥ የማያስገኙም አሉ ። ለሰዎች ሐቀኛ መሆን ዞሮ ዞሮ ውጤት ያስገኛል ። በአንጻሩ ደግሞ ፡ ምናልባትም ከልምድ እንደምታውቀው ፡ ሐቀኛ አለመሆን በመጨረሻ በሰዎች ዘንድ መተፋትን ያስከትላል ። ይህን ያህል ግልጽ ነው ።»

«የአመራርዎ ስልት ኃይል ከየት እንደሚመነጭ አሁን ታየኝ — ለሰዎች እንክብካቤ ያደርጋሉ» አለ ወጣቱ ።

«አዎን ፥ ሰዎቼን እንከባከባቸዋለሁ» አሉ ሥራ አስኪያጁ በቀጥታ ።

ወጣቱ ይህን ዐይነተኛ ሥራ አስኪያጅ በመጀመሪያ ቀርቦ በሚያነጋግርበት ጊዜ ቁጡ ሰው መስለው እንደ ታዩት ትዝ አለው ።

እንዲያውም በልቡ የሚያስበውን ሥራ አስኪያጁ የሚያውቁበት መሰለው ።

«አንዳንድ ጊዜ» አሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ



አስኪያጁ ፡ «ኃይለኛ መስለህ ለመታየት መሞከር አለብህ ። እና እኔ እንዲያ ነኝ ። ድክመት ሲያጋጥመኝ በዋዛ አላልፍም — ግን የማተኩረው ድክመቱ ላይ ብቻ ነው ። ሰውዬውን ፈጽሞ አልጫነውም ።»

ወጣቱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁን ወደዳቸው ። ሰዎች ለምን ከርሳቸው ጋር መሥራት እንደሚወዱም ለመገንዘብ ቻለ ።

«ምናልባት ይህ ያስደስትዎት ይሆናል» አለ ወጣቱ ። በማስታወሻ ደብተሩ ላይ የጻፈውን እያመለከታቸው ፥ «ግቦች — የአንድ ደቂቃ ግቦችና ውጤታቸው ፥ ሙገሳዎችና ግሣፄዎች በሰዎች ላይ ያሏቸውን ተጽዕኖ እንዲያስታውሰኝ ብዬ ያዘጋጀሁት መርሕ ነው ።»

«ግቦች ሒደቶችን ያመነጫሉ ፤
ውጤቶች ሒደቶችን ይቆጣጠራሉ ።»

«በጣም ጥሩ ነው!» በማለት ሥራ አስኪያጁ ሙከራውን አደነቁለት ።

«ወደዱልኝ?» አለ ወጣቱ ሙገሳቸውን እንዲደግሙለት ፈልጎ ።

«ሰማህ» አሉ ሥራ አስኪያጁ የሚሉትን ለማጠናከር ድምጻቸውን ዘለግ አድርገው ፥ «በሕይወቴ የቴፕ ሪኮርደርነት ሚና እንዲኖረኝ አልሻም ። የተናገርኩትን ያለ ማቋረጥ ለመደጋገም ጊዜ የለኝም።»

ሙገሳ አገኛለሁ ብሎ ሲያስብ ፥ ወጣቱ ለሚፈራው ለአንድ ደቂቃ ግሣፄ የተጋለጠ መሰለው ።

ግን ንቁው ወጣት ያልደነገጠ በመምሰል «ምን አሉኝ?» ሲል ጠየቃቸው ። ላፍታ ያህል ትኩር ብለው ተያዩና መሣሣቅ ጀመሩ ።

«አስደስተኸኛል ። እዚህ ሥራ ብትጀምር ምን ይመስልሃል?» በማለት ሥራ አስኪያጁ ጠየቁት ።

ወጣቱ ማስታወሻ ደብተሩን አስቀመጠና በአድናቆት ትኩር ብሎ ሥራ አስኪያጁን እየተመለከተ ፣ «ለእርስዎ እንድሠራ ነው የሚሉኝ?» ሲል በጉጉት ስሜት ጠየቃቸው ።

«አልወጣኝም» አሉት ፤ «በመሥሪያ ቤቴ ውስጥ ያሉት ሌሎች ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ለራስህ ነው የምትሠራው ። ማንም ሰው ለማንም አይሠራም ። ሰዎች የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ እየረዳኋቸው በሒደቱ ድርጅታችንን ይጠቅማሉ ።»

ይኸው ነው ወጣቱ ለብዙ ጊዜ ይመኘው የነበረው ።

«እዚህ ለመሥራት እፈልጋለሁ» አለ ወጣቱ ።

እንዳለውም ለተወሰነ ጊዜ ሠራ ።

ሥራ አስኪያጁ ያዋሉለት ጊዜ ፍሬ አስገኘ ። ምክንያቱም በመጨረሻው ሕልሙ እውን ሆነለት ።



## ወጣቱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ሆነ

የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያ ጅ የሆነውም በማሰቡ ወይም በማውራቱ ሳይሆን መሥራት በመቻሉ ነው ።

የአንድ ደቂቃ ግብ ቀየሰ ።
የአንድ ደቂቃ ሙገሳ አበረከተ ።
የአንድ ደቂቃ ግሣፄ ሰነዘረ ።

አጭርና ቁምነገር ያላቸውን ጥያቄዎች ጠየቀ ፤ እቅጩን ተናገረ ፤ ሣቀ ፤ ሠራ ፤ ተደሰተ ።

እናም ፣ ምናልባት ከሁሉም የሚልቀው ፣ የሥራ ባልደረቦቹ የእርሱን ፈለግ እንዲከተሉ ማበረታታቱ ነበር ።

በሥሩ ላሉት ሰዎች በቀላሉ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን የሚያስችላቸው የኪስ ማስታወሻ አዘጋጀላቸው ። ለተጠሪዎቹም ሁሉ ያንን በስጦታነት አበረከቱላቸው ።

# የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ማስታወሻ

## አጭር ማጠቃለያ

ከፍተኛ ውጤት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደምታገኝ ፤
ለራስህና ለሌሎች የምታበረክተው «ስጦታ»

ግቦች ቀይስ ፤ ሒደትን አሞግስ ፤ ገሥፅ ፤ ሰዎችን አበረታታ ፤

እውነት ተናገር ፤ ሣቅ ፤ ሥራ ፤ ተደሰት ፤

ካንተ ጋር የሚሠሩት ሁሉ ያንተን ፈለግ እንዲከተሉ ጥረት አድርግ ።





## ለራስህ የሚቀርብ ስጦታ

ከብዙ ዓመታት በኋላ ፡ መለስ ብሎ የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራርን መሠረተ ሐሳቦች ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማበትን ወቅት አስታወሰ ። ከዚያን ወዲህ ረጅም ዘመን ያለፈ መሰለው ። ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ የቀሰመውን በማስታወሻው ላይ መመዝገቡ ደስ አለው ።

ማስታወሻዎቹን በመጽሐፍ መልክ አሰባስቦ ለብዙ ሰዎች አደለ ።

ወይዘሮ ጆንስ አስታውሳው የደወለችለት ትዝ አለው ፤ «ምስጋናዬን ለመግለጽ ቃላት ያጥሩኛል ። እርዳታህ በሥራዬ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቶልኛል ።»

ስለ አለፈው ሲያስብ ፈገግ አለ ። ከአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጁ ምን ያህል እንደ ተማረ አስታወሰና ባለውለታነታቸውን ተገነዘበ ።

እርሱው ራሱ ፡ አዲሱ ሥራ አስኪያጅ ፡ የቀሰመውን የአመራር ዕውቀት በአንድ እርከን ወደፊት ለማራመድ በመቻሉ ደስ አለው ። የጽሑፉን ግልባጮች በድርጅቱ ውስጥ ለሚገኙ ለሌሎች ብዙ ሰዎች በማደል አያሌ ጉልህ ችግሮችን መፍታት ቻለ ። ከእርሱ ጋር የሚሠሩት ሁሉ ደኅንነት ተሰማቸው ። እያንዳንዱ ሰው ከመጀመሪያው ምን እንደሚሠራና ለምን እንደሚሠራ ስለሚያውቅ መወናበድ ወይም ሥጋት አይሰማውም ።

በተጨማሪም ቀላል የሚመስሉት የአንድ ደቂቃ ሥራ አመራር ስልቶች የግብ ቅየሳ ፡ ሙገሳና ግሣጼ ለምን የሚፈለገውን ውጤት እንደሚያስገኙ እያንዳንዱ ለመረዳት ቻለ ።



የመጽሐፉን ቅጅ ያገኘ ሰው ሁሉ መልእክቱን በጥቅም ላይ ማዋል እስኪችል ድረስ በራሱ ፍጥነት ደግሞ ደጋግሞ አነበበው ። ሥራ አስኪያጁም አዲስ ነገርን ለመልመድ መደጋገም ምን ያህል ተግባራዊ ጥቅም እንዳለው በሚገባ ዐውቋል ፤ አሳውቋል ።

በዚህ በቀላልና ሐቀኛ መንገድ ዕውቀቱን ማካፈሉ ጊዜውን ቆጠበለት ። በእርግጥ ሥራውንም አቃለለለት ።

በሥሩ ከነበሩት ሰዎች ብዙዎቹ ራሳቸው የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጆች ሆኑ ። እነርሱም በበኩላቸው ይህንኑ ለበታቾቻቸው አስተላለፉ ።

መላው ድርጅት የበለጠ ውጤታማ ሆነ ።

አዲሱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲያስብ ፡ ምን ያህል የታደለ ሰው መሆኑ ተሰማው ። ከፍተኛ ውጤት በአነስተኛ ጊዜ ውስጥ የሚያስገኝለትን ስጦታ ራሱ ለራሱ አበረከተ ።

ለማሰብና ለማቀድ ፡ ለድርጅቱም ተገቢውን ርዳታ ለመስጠት ጊዜ አገኘ ።

ሰውነቱን ለማፍታታትና ጤንነቱን ለመጠበቅ ጊዜ አተረፈ ። ሌሎች ሥራ አስኪያጆች በየዕለቱ ራሳቸው ላይ ከሚጠመጥሙት የመንፈስና የአካል ጭንቀት እንደ ተላቀቀ ታወቀው ። ከርሱ ጋር ከሚሠሩት ሰዎች ብዙዎቹ ተመሳሳይ ጥቅሞች እንዳገኙ ታየው ።

የእርሱን መሥሪያ ቤት የሚለቅ ሠራተኛ ወይም ከሥራ ገበታው የሚጠፉ ሰው ቁጥር እየቀነሰ መጣ ።

ጠቀሜታው ከፍተኛ ሆነ ።

ከመቀመጫው ተነሥቶ በንጹሕ ቢሮው ውስጥ ወዲያና ወዲህ መንጐራደድ ጀመረ ፤ በጥልቅ ሐሳብ ተውጦ ። በማንነቱና በሥራ አስኪያጅነቱ እርካታ ተሰማው ።

ሰዎቹን መንከባከቡ በሚገባ ጠቅሞታል ። በድርጅቱ ውስጥ እያደገ ፤ የበለጠ ኃላፊነትና ክፍያ እያተረፈ ሔደ ።

የወጣለት ሥራ አስኪያጅ መሆኑን ተገነዘበ ። ምክንያቱም ድርጅቱና የሥራ ባልደረቦቹ በይፋ የተጠቀሙት በእርሱ መኖር መሆኑን ተረዳ ።



## ለሌሎች የሚሰጥ ስጦታ

የቢሮው የውስጥ ለውስጥ መገናኛ በድንገት አቃጨለና ከጥልቅ ሐሳብ ቀሰቀሰው ። «ይቅርታ ያድርጉልኝ በማቋረጤ» አላቸው ጸሐፊው ፤ «አንዲት ወጣት ልታነጋግርዎት መስመር ላይ ነች ። በድርጅታችን ውስጥ ሰዎችን እንዴት እንደምንመራ ለመረዳት ስለምትፈልግ ፤ ቀጠሮ ሊሰጥዋት ይችሉ እንደ ሆን ትጠይቃለች ።»

አዲሱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ደስ አለው ። ብዙ ሴቶች ወደ ሥራ ዓለም መግባታቸውን ያውቃል ። እናም ከመካከላቸው አንዳንዶቹ እርሱ እንዳደረገው ሁሉ ስለ ጥሩ ሥራ አመራር ለማወቅ መጓጓታቸው አስደሰተው ።

አሁን የርሱ መሥሪያ ቤት በተሳካ ሁኔታ ይንቀሳቀሳል ። እንደምትገምቱት በዓለም ውስጥ አሉ ከሚባሉት ከመሰል ድርጅቶች አንዱ ሆኗል ። የክፍሉ ሠራተኞች ምርታማና ተደሳቾች ናቸው ። እርሱም ተደሳች ነው ። በእርሱ ቦታ መሆንን ያስመኛል ።

«በሚመችሽ ጊዜ ነው» ብሎ ለደዋይዋ ሲመልስላት ኩራት ተሰማው ።

ከጥቂት ቀናት በኋላም ከአንዲት ብልህ ወጣት ጋር ውይይት አደረገ ።

«የሥራ አመራር ምሥጢሮቼን ሳካፍልሽ ደስ ይለኛል» አላት አዲሱ የአንድ ደቂቃ ሥራ አስኪያጅ ፤ እንግዳዋ እንድትቀመጥ መቀመጫ እያሳያት ። በቅድሚያ አንድ ነገር ብቻ እንድትፈጽሚልኝ እጠይቅሻለሁ ።»

«ምን ይሆን?» አለች እንግዳዋ ።

«ቀላል ነው» አላት ሥራ አስኪያጁ ። «የሚከተለውን ምክሬን ተቀበይኝ ።

«እንቺም ዕውቀትሽን ለሌሎች አካፍይ»

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋው ብር 2.50